ההסתדרות

ביחד, בשבילך

אגף הרווחה

רשות ההסתדרות לצרכנות

# ሸማቾች፣
# መብታችሁን ዕወቁ!

## ለእስራኤላዊ ሸማች መመሪያ



አዘጋጅ፡ የህግ ጠበቃ አሪኤል መላአሂ

መብቶች ሁሉ ሂስታድሩት በሠራተኞች የሸማቾች ፌድራሲዮን የተጠበቁ ናቸው፤

የመስራቤት ቡድን፡ የህግ ጠበቃ ያሮን ለቪንሶነ፣ ራሔል ካርሶ፣ ዳፍና ሐር ኤቬን፣ ዕዝራ ጊናቲ

የህግ አማካሪዎች፡ኤራን-መላአሂ የጠበቃ መ/ቤት፣ የህግ ጠበቃ ቫጊፍ ኤሊአቭ

ለሦስተኛ ጊዜ ታርሞ የተዘጋጀ፣ ቴል አቪቭ-ያፎ፣ 2015 ዓ.ም

እዚህ የቀረበው  መረጃ አጠቃላይ ስለሆነ የህግ አማካሪው የሚሰጠውን አይተካም  ያለ ተስማሚ ጠበቃ አማካሪ በቀር መደገፍ አያስፈልግም፡፡ በመመሪያው  ያለው መረጃ በማርች 2015 የተስተካከለ ነው፤ ወሳኙ ህጉና መመሪያው ነው፡፡ የተስተካከለ መረጃ ለማግኘት በwww.histadrut.org.il ድኅረ ገፅ የኢንተርኔት አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡፡

# የአዲሱ ሂስታድሩት ድርጅት ሊቀ መንበር ምረቃ

## የሂስታድሩት ሴቶችና ወንዶች ድርጅት አባላት

የሂስታድሩት ማኅበር የተዳከሙትን ሕብረተሰብ በማጠንከር በእስራኤል ኅብረተሰብ እኩልነት እንዲሰፍን በተለያየ አቅጣጫ ይሠራል፤ የሠራተኛውን መብቶችና ደረጃውን በማጠናከር ይጀምርና አገር አቀፍ ለውጥን ለማምጣት የሠራተኛውንም የሸማችነት መብት እስከ ማስከበር ይሄዳል፡፡

ሂስታድሩት በሠራተኞች የሸማቾች ባለሥልጣን አማካይነት በእስራኤል ለሸማቹ ማኅበረሰብ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የሸማቾች ባለሥልጣን በህግ ታዋቂነት ያለው ሲሆን በእስራኤል የመንግሥት ድርጅት ያልሆነ ታላቅ ድርጅት ነው፤፤

መረጃን ማግኘትና የመብቶችን ዕርዳታ ማግኘት ለተጨማሪ ዕይታ ትርጉም ላለው ተግባር ዕድገት መሠረት ይሰጣል፡፡ ከሂስታድሩት የሸማቾች ፌድሬሽን ባለሥልጣን ለሸማቹ ጥቅምና በሸማቾች መብት ጉዳት እንዳይደርስ ክትትል በማድረግ ህግ እንዲደነገግ ይገፋፋል፡፡ ጉዳት የደረሰባቸውን ሸማቾችም ይረዳል፡፡

የመመሪያው ዓላማ: ጠቃሚ መረጃን ለሸማቾች ለማቅረብ ነው፡፡ የሸማች ዕውቀት ከሚነገርላቸው አንዱ የለውጥ መሣሪያና የታጣውን ዕኩልነት ለመቀነስና በእስራኤል ማኅበረሰብ ልዩነትን ለማሳነስ ነው፡፡

ከአክብሮት ጋር፣

**አቪ ኒሳንኮሬን**
የአዲሱ ሂስታድሩት ሊቀ መንበር

## ውድ ሸማቾች፣

ዓመታት ባለፉ ቁጥር በእስራኤል ስለሸማቾች ህግ መደንገግ እየተሻሻለ ሂዷል፤ በእስረኤል ስለመብቶቻቸቸውና መብቶቻቸውን ስለመጠቀም የሸማቾች ዕውቀት ግን እንዲህ አይደለም፤ በህጉ በሸማቹ መብቶችና ስለእኒህ መብቶቹ ሸማቹ ያለው ዕውቅና በተቃራኒው ታላቅ ልዩነት ሲኖረው ከሂስታድሩት የሸማቾች መብት ተከላካይ ፌድሬሽን ሥላጣን በዕለት ዕለት ሥራችን ምስክሮች ናቸው፡፡ ስለዚህም እንደዚህ ዓይነት መመሪያ መኖር በጣም አስፈላጊነት አለዉ፡፡ በነገሩ ሁሉ የእውቀት ልዩነታችሁን ያሳንሳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ህጉ በሚሰጣችሁ የመሸማመት መብቶች የእናንተን ሓይልና እዉቀትነት፡ ያዳብራል ብለን በማመን፡ ነገር ግን፡ በዚህ መግለጫ የሸማችን መብት ሙሉ በሙሉ መሸፈን አይችልም፡፡ ስለዚህ በጣም ከፍተኛ ዋና ዋና ናቸው ያልናቸውን ርዕሶች በመምረጥ አትኩረናል፡፡ ተስተካክሎ የቀረበው መረጃ ለትክክለኛ ሸማችነት ዕውቀት አድማሳችሁን ከፍ እንደሚያደርግና በእስራኤል የሸማችን መደብ እንደሚያሻሽል እርግጠኞች ነን፡፡

ከአክብሮት ጋር፣

**የህግ ጠበቃ አብርሃም ሚኃኤሊ**
የሂስታድሩት ማኅበራዊ ክፍል ሊቀ መንበር

**የህግ ጠበቃ ያሮን ከቪንሶን**
የሸማቾች ፌድሬሽን ሥልጣን ዋና ሥራ አስኪሃጅ

## ማውጫ


**የኢዲሱ** የሂስታድሩት ማኅበር ሊቀ መንበር ባርኮት 3

የሂስታድሩት የሸማቾች ሥልጣን 7

ሻጭና ሸማች 8

የሸማቾች አሥርቱ ቃላት 8

**ሸማችን ማሳሳት መከልከሉ** 9

ተቀባይነት የሌለው ተፅዕኖ 9

የተከለከሉ ማስታወቂያዎች 9

ሲያሳሳቱን ወይም ሲጠቀሙብን ምን ማድረግ አለብን? 9

**ሙሉና ትክክለኛ መረጃን የመቀበል መብት** 10

ምርቶችን ምልክት የማድረግ ግዴታ 10

ዋጋን የማሳየት ግዴታ 10

ዋጋን የማሳወቅ ግዴታ 11

ምርቶችን ስለማስመለስ መመሪያውን ግልፅ ማድረግ 11

ውሎችንና ግዥን በተመከተ ሌሎች ሠነዶችን የመመልከት መብት 11

ግልፅ ሠነዶች 11

ምርቶችን የአጠቃቀም መመሪያዎች 12

ዋጋን ከፍ ማድረግ መከልከሉ 12

**ገብያን ማፍረስ** 13

ምርቱ ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም ጉድለት ሳይገኝበት ገበያን የማፍረስ መብት 13

ገቢያን የማፍረስ መብት የማይመለከታቸው ልዩ ሁኔታዎች 16

ገቢያ በመፍረሱ ክፍያን ማስመለስ 16

ገቢያን ለማፍረስ የሚከፈል ክፍያና ሌላም፡ ሻጩ ለሸማቹ ተመላሽ ከሚያደርገው ምን የመቀነስ መብት አለው? 17

ሥጦታን ስንቀበል የማፍረስ መብት 17

የርቀት ገቢያን ማፍረስ 18

የሸቀጥ ገበያን ማፍረስ 19

የጊዜ ገደብ ስላላቸው የተወሰኑ ገቢያዎች ልዩ መመሪያዎች 20

የመናፈሻ ቦታዎች 20

የሰውነት ማዳበሪያ(ጂም) ተቋማት 21
ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም በጉድለት ምክንያት ገቢያን ማፍረስ 22
**ኃላፊነትና አገልግሎት** 22
ኃላፊነት 22
ነፃ የስልክ አገልግሎት 23
**አንድ ዓይነት ውሎች** 24
**የመክፈያ መንገዶችን በአግባብ መጠቀም** 25
ቸኮች 25
ክሬዲት ካርዶች 25
የመግዣ ኩፖኖች 26
በመግዣ ኩፖን(ታቭ ክንያ) የተገዛን ዕቃ መመለስ 27
የማስተዋወቂያ ስጦታ ቫውቸር 27
**የበረራ አገልግሎትን በተመለከተ ልዩ መመሪያዎች** 27
ጥቅሞችና ካሣዎች 28
ካሣ እንዲደርሰን የሚያደርጉ ሁኔታዎች 30
የማሳወቅና ዕርዳታ ግዴታዎች 32
ምሳሌ ካሳዎች 32
**የትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት** 33
የትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ሥልጣን 33
ከጠበቃ ጋር ወይም ያለ ጠበቃ? 33
ክሱን የት እናቅርብ? 33
ቀረጥ መክፈል 33
የክሱ መመሥረቻ፣ መከላከያና የፍርድ ቤቱ ሂደት 34
የይግባኝ ሥልጣን 34
**የትና ለማን እናመለከታለን?** 34
**የሸማች ህግ ድንገጋ** 36
**መ/ቤቱና ቅርንጫፎቹ** 38

## ለሸማቾች የሒስታድሩት ማኅበር ሥልጣን

የሸማችን ጥቅም መከላከል: የሠራተኛውን የገቢ ምንጭና መብቶቹን ከማስጠበቅ ጋር ተለይቶ የማይታይ ስለሆነ መገበያየትን ማጠናከር እንዳለበት የሂስታድሩት ድርጅት በመጀመሪያ ላይ ነበር ያስተዋለው።

የሂስታድሩት ለሸማቾች "ከየሂስታድሩት መብት ተከላካይ" በሚል ስም በ1970 ተቋቋመ። በ1982 በወጣው አንድ ወጥ ህግ፣ በ1984 በወጣው የፍርድ ቤት ህግ(የውኅደት ህግ)፣ በ1988 በወጣው ንግድን በሚወስነውና ህግና በ2006 የክስና የወኪል ህግ መሠረት በ1970 ዓ.ም. ተቋቋመ። በ1982 ዓ.ም. የፍርድ ቤቱ ህግ(የተጠናከረው) በ1984፣ አንድ ወጥ ህግ መሠረት በሠራተኞች የሸማቾች ድርጅት በመባል በ1983 ዓ.ም. በሃገሪቱ ዕውቅና ተሰጠው።

ድርጅቱን በበላይነት የሚመራ ዋና አስተዳዳሪ ሲኖረው መ/ቤቱ ደግሞ ቴል አቪቭ በሚገኘው የሂስታድሩት የሠራተኞች ድርጅት ውስጥ ይገኛል፤ አብዛኛው የሠራተኞች ድርጅት እንቅስቃሴ በመላ አገሪቱ ተሰራጭተው በሚገኙ ብዙ የሂስታድሩት ሠራተኞች ስለሸመታ ዕውቀት ያላቸውና በዚሁ መስክ ትምህርት በቋሚነት የሚከታተላሉ ሠራተኞች አማካይነት ይከናወናል።

እንደ የቤት ዕቃዎች፣ የግንኙነት ካምፓኒዎች(የተንቀሳቃሽ ስልክ ኩባኒያዎች፣ ኢንተርኔት፣ የኬብልና የሳተላይት)፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች፣ አልባሳትና ጫማዎች፣ መዝናኛና ቱሪዚም፣ የጂምናስቲክ መሥሪያዎች፣ የትምህርት ኮርሶች፣ በመንገድ ወይም የሸቀጥ ገቢያ፣ ከርቀት በሚደረጉ መገበያየቶች(በስልክ፣ በኢነተርነትና ወ.ዘ.ተ) በመሳሰሉት ዓመቱን ሙሉ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ማመልከቻዎችን ለሸማቾች መብት ተከላካይ ባለስልጣን ድርጅት ይንከባከባል።

ለሸማቾች መብት ተከላካይ ባለስልጣን ድርጅት ተወካዮች ስለሸመታ ህግ በፓርላማ ከሚደነግጉ ኮሚቴዎች ፊት በቋሚነት እየቀረቡ የሸማቾችን ጥቅም በማስጠበቅ የሸማች ህግን ያራምዳሉ፤ እንዲሁም በጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም ባለሙያዎችና ከድርጅቱ በበጎ ፈቃደኝነት ሰዎች እየተገኙ በልዩ ልዩ ጥራት ወሳኝ ተቋም የደኅንነት ኮሚቴዎች በመገኘት ለተጠቃሚው ጥራትን ያስጠብቃሉ። የድርጅቱ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የሸማቾችን በሚከላከሉ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ኮሚቴዎች ይሸማሉ።

ድርጅቱ ሸመታን ወይም ገቢያን በሚመለከት ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲይዝ ለማድረግ በተለያዩ መስኮች ስለገቢያ ምርመራንና ጥናቶችን በማካሄድ ለሰፊው ሕዝብ ምክር ያቀርባል።

## ሻጪና ሸማች

በእስራኤል ለሸማች የሚከላከሉ ብዙ ህግጋት አሉ፤ ዋና የህግጋትንና የመመሪያዎችን ሙሉ ዝርዝር በገፅ 36 ማግኘት ትችላላችሁ፤ በጣም አስፈላጊ ከሚባሉት ህግጋት ዋናው "ሸማችን መከላከል ነው፤" (ሃጋናት ሃጻርሃን)፤ በዚህ ህግ የሸማቾችን ልዩ ልዩ መብቶችና ግዴታዎችን የሚወስኑ ብዙ መመሪያዎችን አጠቃሎ የያዘ ይሁን እንጂ እነህ መብቶችና ግዴታዎች በባለ "ሻጩና" "በሸማቹ" መካከል ያለ ግንኙነትን ብቻ እንደሆነ ማስታወስ ይኖርብናል፡፡

ለሸማች የሚከላከለው ህግ "ሻጭ" እና "ሸማች" ማን እንደሆኑ ያብራራልናል፤ "ሻጪ" ምርትን የሚሸጥ ወይም አገልግሎት አቅራቢ አምራችንም ጨምሮ እንደሆነ ይገልጸዋል፤ እንደ ሥራ በቋሚነት ንብረትን የሚሸጥን አገልግሎትን የሚያቀርብን እንጂ በፈቀደ ንብረት የሚሸጥን ወይም አገልግሎት የሚሰጥን እንዳልሆነ ልብ ማለት እንዳለብን የሸማች ተከላካይ ህግ ያብራራልናል፤ የሸማች ተከላካይ ህግና መመሪያ "ሸማችን" በተሰማራበት ንብረትን የሚገዛ ወይም አገልግሎትን በተለይ ለግል፣ ለቤት ወይም ለቤተሰባዊ ጥቅም ከሻጩ የሚቀበል ሲል ህጉ ያብራራል፡፡ ንብረትን የሚገዛ ወይም አገልግሎትን በተለይ ዋና ጥቅሙ ለግል፣ ለቤት ወይም ለቤተሰባዊ ጥቅም ላልሆነ ለምሳሌ ለንግድ ከሆነ "ሸማች" እንዳልሆነ የሸማች ተከላካይ ህግ ይገልጸዋል፤ የሸማች ህግና መመሪያዎች አይመለከተውምም፤ በሸማች ህግ መሠረት መመሪያዎቹ በሸማቾች በባንኮችና በዋስትና ድርጅቶች መካከል ባሉት ግንኙነቶች ላይም አይመለከተውም፡፡

## አሥርቱ የሸማቾች ቃላት

1. አስቀድመዉ የሚገዙትን ዕቅድ ያውጡ።
2. ከመግዛትዎ በፊት የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን ዋጋ ከተለያዩ ቦታዎች ዋጋ ጋር ያወዳድሩ።
3. ዋጋን በህጉ መምሪያ መሰረት ከሚያሳውቅ ሻጭ ይግዙ።
4. የአምራቹን ስምና አድራሻ ከምርቱ ላይ ያለውንና የኃላፊነት መረጃ ያለውን ምርት ይግዙ።
5. አስተማማኝነቱንና ጥራቱን የሚያረጋግጥ የጥራት መስፈርት ያለበትን ምርት ለመግዛት ይምረጡ።
6. ከመፈረምዎ በፊት ስምምነቶችን ተቀብለዉ ያንብቡ።
7. ዕቃውን ከተቀበሉ በኋላ እንጂ አስቀድመዉ አይከፈሉ፣ የከፈሉበትንም ደረሰኝ ተቀበሉ።
8. በአጋጣሚ በመንገድ ላይ ወይም ወደ ቤትዎ ከሚመጡ ሰዎች ከመግዛት ይቆጠቡ።
9. የክሬዲት ካርድን ዝርዝር በስልክ ወይም በኢንተርነት ለማያውቋቸው አካላት ከመስጠት ይቆጠቡ፤ በኢንተርኔት ሲገዙ ድህረ ገፁ አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጡ።
10. ወደፊት ለሚከፈሉ ቸኮች ላይ ለተቀባዩ ብቻ ብለው ይጻፍበት፤ "ለ.... ከፈሉ"(ካለ) የሚለውን ይሰርዙ በኤክስም ምልክት(ሁለት ሰያፍ መስመሮች አድርግባቸው)፤ የባንኩን ሠራተኛ በመጠየቅ የተዘጋጁ ቸኮችን አስቀድሞ ማዘዝ ይቻላል።

## ሸማችን ማሳሳት መከልከሉ

ነጋዴ ወይም ሻጪ ለሸማች በሚያስተላልፈውም ይሁን ወይም በፊቱ በሚያቀርበው መረጃ እንዲሁም መረጃን በመደበቅ በማንኛውም መንገድ ማሳሳት የተከለከለ ነው፡፡ ሸማቹን ማሳሳት የሌለበትን ዋና ዋና ምሳሌ ህጉ ያቀርብልናል፤ ከእነዚህም መካከል፡ ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን የሚያስረክብበት ጊዜ፣ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ዓይነት፣ የዕቃው ሚዛን፣ የተመረተበት ቦታ፣ የአገልግሎት ሰጪውን ማንነት፣ ለጥገና ተለዋጭ ዕቃ ስለመኖራቸውና ሌላም። እኒህ ርእሶች መላዉን ሁኔታዎች አይደመድሙም። ተጨማሪ ሁኔታዎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የተሳሳተ መረጃን ወይም መረጃን አለመስጠት እንደማሳሳት ይቆጠራል፡፡

## ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖ

ዕቃ ሻጩ ሸማቹ ላይ የግንኙነት ነፃነቱን የሚከለክል ተገቢ ያልሆነ ተፅዕኖ ማድረግ የለበትም። ሸማቹን የሚከላከል ህግ ቁጥር 3 ሸማቹን የሚያዘናጉ ተገቢ ያልሆኑ ዝርዝር ሁኔታዎች አሉ፤ ለምሳሌ ሸማቹ ቦታውን ለቆ እንዳይሄድ ማድረግ፣ እንዳይመካከር መከልከል፣ ገዢን ለማሳመን: ሸማች: ግንኙነት የመቆጠብ: ፍላጎቱን እየገለፀ: ከቤቱ እቃ እንዲገዛ ደጋግሞ መምጣት: ሸማች: ከግዥ ቦታ ተመልሶ እንዳይመጣ መከልከል፣ ሸማቹ ቋንቋ አለማወቁን መጠቀም፣ መዛት ወይም ማስፈራራት ወይም የማይገባውን አገልግሎት ክፍያ መጠየቅና ሌላም፡፡

## ክልክል ማስታወቂያዎች

እንደተባለው፤ ሻጭ ሸማቹን በማንኛውም መንገድ ማሳሳት የለበትም፤ በማስታወቂያዎች ማሳሳት ተደጋግሞ የሚከሰት ድርጊት ስለሆነ ህጉ በግልፅ ወስኗል፤ ስለዕቃውና ዓይነቱ በማስታወቂያ ማሳሳቱ ብቻ ሳይሆን የሚያሳስት ማስታወቂያ መኖሩንም ይከለክላል፡፡ የሚተላለፈው መረጃ እውነትነት ያለበት ቢሆንም በግልፅ ሳይነገር ማስታወቂያው መልኩን ቀይሮ እንደ ጽሁፍ መቅረብ የለበትም፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጋዜጣ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት ወይም በትልልቅ ሠሌዳዎች በመንገድ አካባቢ በሚለጠፉ በማስታወቂያ ልዩነት የለውም፡፡ በተጨማሪም ወጣቶች ላይ ያተኮረ ማስታወቂያዎች ወይም ንግድ ስልት በወጣትነታቸው የተነሳ በቀላሉ የሚያምኑ በመሆናቸዉ ያለ አግባብ መጠቀም ወይም መበዝበዝ ክልክል ነው፡፡

## ሲያሳስቱን ወይም ሲጠቀሙብን ምን እናድርግ?

ሸማች፤ ዕቃ ወይም አገልግሎት ከገዛ በኋላ እንዳሳሳቱት ወይም እንዳታለሉት ከተረዳ በተወሰኑ ሁኔታዎች ገቢያውን እንዲሠርዝ የሸማቾች ህግ ይረዳዋል፡፡ እንዳታለሏችሁ ወይም እንደ ተጠቀሙባችሁና መሠረዝ ይቻላልንን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ቀላል አይደለም፤ ስለዚህም ከመሠረዝ በፊት አስቀድሞ ተገቢ ምክር መቀበል ይገባል፡፡ እንዳታለሏችሁ ወይም እንደተጠቀሙባችሁ ከተሰማችሁ በመላ ሃገሪቱ ወዳሉት የሂስታድሩት የሠራተኞች ድርጅት ወይም ቴል አቪቭ ወደ ሚገኘው የሠራተኞች ድርጅት ዋና መ/ቤት በማመልከት ምክርና መመሪያ መቀበል ትችላላችሁ፡፡ (ዝርዝሩን በገፅ 38 ይመልከቱ)

## ምርቶችን ምልክት የማድረግ ግዴታ

በህጉ መሠረት ማንኛውም በሃገር ዉስጥ የሚመረት ምርት ሁሉ ምልክቱ በዕብራይስጥ ቋንቋ መደረግ አለበት፡፡ ከሃገር ውጭ ተመርቶ የሚገባ የሚመረት ምርት በዕብራይስጥ ምልክት መደረግ አለበት፤ ምርቶች ሁሉ እንዲታይና እንዲነበብ ግልፅ ሆነው ምልክት እንዲደረግባቸው ግድ ነው፡፡ ምርቶች ላይ መጻፍ ካለባቸው ነገሮች መካከል ስሙና የያዘው ንግዳዊ መጠሪያ፣ ምርቱ አዲስነቱን ጉድለቱን ወይም ሁለተኛ ደረጃ መሆን አለመሆኑን፣ የአምራቹን ስምና አድራሻውን፣ ምርቱ ወደ ሃገር የመጣ ከሆነ የአስመጪው ስምና አድራሻ፣ የተመረተበትን ሃገር መጠቀስ አለበት፤ በተጨማሪም ዋጋቸው በመንግሥት ቁጥጥር ለሆኑ ምግብ ነክ ምርቶች ከፍተኛ ዋጋቸውንና ዋጋዉ በመንግሥት የወሰነ መሆኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡

## ዋጋን የማሳየት ግዴታ

ዋጋን ማሳየት በነጋዴዎች ላይ ከተጣሉት ዋና ግዴታዎች አንዱ ነው፤ በህጉ መሠረት ዋጋ በዓይን በሚታይ ቦታ ላይ፣ ግልፅና ተነባቢ መሆን አለበት፤ ዋጋው በእስራኤል ገንዘብ መሆን ይኖርበታል፤ በውጭ ምንዛሬ ዋጋን ማሳየት ክልክል ነው ሸማች በቅናሽ የሚከፍል እንዳይመስለዉ፡፡ አገልግሎት ከእስራኤል ውጭ መሰጠት ካለበት ወይም ከእስራኤል ውጭ ለሚሸጥ ምርት ዋጋውን በውጭ ምንዛሬ ማሳየት ይቻላል፡፡

የሚታየው ዋጋ ሸማቹ የሚከፍለው የመጨረሻ ዋጋ መሆን አለበት፤ ዋጋው፤ ቫት ወይም ተጨማሪ ግብርን ወይም ሌላ ከምርቱ ላይ መጨመር ያለበት ግብርን ሁሉ ማጠቃለል አለበት፤ ለምርት የቀረቡና ርክክቡ በመላክ ለሚደርሱ ምርቶች ምርቱን የገዛው ከመክፈል የሚቆጠብበት መንገድ ከሌለው በቀር፤ የተገለጸው ዋጋ መላኪያውንም የጨመረ መሆን አለበት፡፡

ለምግብ ቤቶች፣ ለክለቦችና ለመሳሰሉት ለሸማቹ ለጥበቃ የሚሆን ወይም ጉርሻ(ቲፕ) ከተገለጸው ዋጋ ተጨማሪ ዋጋ መጠየቅ የለበትም፤ ይፋ የሆነው ዋጋ ምርቱን የገዛው የሚከፍለው የመጨረሻ ዋጋ ነው፤ ቲፕ መስጠቱ በገዢው ነፃ ፍላጎት የመነጨ መሆን ይኖርበታል፡፡

በተጨማሪም መጠናቸውን በህግ ወይም በታወቀ መመሪያ ማሳወቅ ያለባቸውና በጅምላ ስለሚሸጡ ወይም አስቀድመው ለታሸጉ ምርቶች ለአንድ መለኪያ መሠረት ዋጋቸው መጠቀስ ይኖርበታል፤ ለአንድ መለኪያ ማለት፣ እነደአስተያየቱ፣ 1 ኪሎ ግራም፣ 1ሊትር፣ 1ሜትር፣ የምርቱ 1 ካሬ ሜትር፣ 100 ግራም ወይም 100 ሚሊ-ሊትር፤ ለምሳሌ ምርቱ አስቀድሞ 1.5 ኪሎ ግራም ከታሸገ አጠቃላይ ዋጋውንና የ1 ኪሎ ግራም: ዋጋን መጠቀስ አለበት፤ በጅምላ ስለሚሸጡ ምግብ ነክ ምርቶች፣ ያልታሸጉና በትልቅ መያዣ የሚሸጡ ምርቶች ለየት ይላል፡፡

## ዋጋን የማሳወቅ ግዴታ

ልትቅ ቸርቻሪ(ታላላቅ እንደ ምግብ አውታረ መረቦች _ሱፐር ማርኬቶች ያሉት) የሆነን በኢንተርኔት አማካይነት በሶቆቹ ያሉትን ምርቶች ዋጋ እንዲያሳውቅ ህጉ ያስገድደዋል፤ ዋጋዎች በነጋዴው ድህረ ገፅና በሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን ድኅረ ገፅና ለጽድቃዊ ንግድ ይፋ መደረግ አለባቸው፤ ማስታወቂያው ተጠቃሚው ሕዝብ አውርዶ ሊጠቀምበት በሚችል ሁኔታ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ነጋዴው ፋይሉን አድራሻውንና ሱቆቹን ሁሉ በሱቁ የምርቶችን ዋጋ ያስታወቀበት ሱቅንም የሚገልፅ በተጨማሪ ፋይል የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ ስለምርቱ ዝርዝር ሁኔታ፣ በሱቅ እንደሚገኙ፣ ዋጋቸውን፣ የአምራቹን ማንነት ወይም አስመጪውና ልዩ አሻሻጥ (ቅናሽ ወይም የጨረታ) መኖሩንና የመሳሰሉትን በፋይሉ መጠቀስ አለባቸው፡፡ በፋይሉ ያሉ የሱቅ ዝርዝር ቢያንስ ከአንድ ቀን በፊት የተስተካከለ መሆን ሲኖርበት የምርቶችና ዋጋቸው ፋይል ቢያንስ አንድ ስዓት በፊት መሆን አለበት፤ ይህ መመሪያ በሜይ 2015 ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ምርቶችን ለማስመለስ መመሪያውን ግልፅ ማድረግ

ማንኛውም ነጋዴ ምርቶችን ስለመመለስ መታወቂያውን በሚታይ ቦታ ግልፅና ለዓይን ተነባቢ በሆነ ሁኔታ፣ በጉድለት ሳይሆን ምርቶችን የማስመለስ መመሪያውን የማሳየት ግዴታ አለበት፤ በጉድለት ምክንያት ሳይሆን ምርትን ሸማቹ ለመመለስ ቢፈልግና ሻጩ ባወጀው መመሪያ ባይቆም ምርቱን የገዛው ሻጩ አልመልስም ካለበት ቀን ጀምሮ በሳምንት ውስጥ የገዛውን ምርት በመመለስ ገንዘቡን የመቀበል መብት አለው፡፡ ምርትን የማስመለስ ማስታወቂያ ከሌለ ሻጩ ጉድለት ተገኝቶበት ሳይሆን ምርቱን ተመልሶ ለመቀበል የሚስማማ እንደሆነ ህጉ ይወስናል፤ ምርትን ማስመለስ የሚቻለው የምርቱ ሁኔታ ሳይበላሽ የተጠበቀ ሲሆን ነዉ። ይኸን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ እሽጉን መፍታት ምርቱ እንደተበላሸ አያስቆጥረውም፡፡

## ውልንና ከግዢ ጋር የተያያዙ ሌሎችን መረጃዎች የመመርመር መብት

ሸማቹ ከሻጩ ጋር ውል ከመፈራረሙ በፊት ውሉን እንዲመረምር ሻጩ ዕድል መስጠት ይኖርበታል፡፡ ከፊርማ በኋላ ሻጩ ለሸማቹ የውሉን ግልባጭ መስጠት አለበት፡፡ ምርትን ወይም አገልግሎትን ሲገዙ የዋስትና ካርድ የሚሰጥበት ሁኔታ ከሆነ፤ ሸማቹ ምርትን ከመግዛቱ በፊት የዋስትና ካርዱን መመልከት መብት አለው። በግዢው ወቅት ሻጩ የዋስትና ካርዱን ግልባጭ ለገዢው መስጠት አለበት።

## ግልፅ ሠነዶች

በልዩ መገበያየት ጊዜ(የሸቀጥ ገብያ፣ ወደፊት የምናያቸውን የርቀት መገበያየትን) ሻጩ ስለመገበያየቱ ዝርዝርና ስለምርቱ ሁኔታና በህጉ ሸማቹ የገዛውን መሠረዝ እንደሚችል በጽሁፍ ለገዢው መስጠት ይኖርበታል፡፡

## ምርቶችን የአጠቃቀም መመሪያዎች

ሸማችን ተከላከይ ህግ: የአጠቃቀም መመሪያ እንዲኖራቸው የሚያስገድዳቸው ምርቶች በሰፊ ተዘርዝረዉ አሉ፤ የአጠቃቀም መመሪያዎች በዕብራይስጥ ቋንቋ መሆን አለባቸው፤ ከውጭ ለመጣ ምርት የአጠቃቀም መመሪያውና (በምርቱ ላይ የሚታዩት ማስጠንቀቂያዎች) በእንግሊዘኛ ከሆነ የተጻፈውን በትክክል ወደ ዕብራይስጥ ትክክልና ግልፅ ሆነው መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡

## ዋጋን ከፍ ማድረግ መከልከሉ

ዋጋቸው በህግ የተወሰነ("በመንግሥት ቁጥጥር ያሉ ምርቶች") አስፈላጊ ምርቶችና አገልግሎቶች አሉ፤ የኸውም ነጋዴዎች ምርቶች አስፈላጊ መሆናቸውን በማወቅ ዋጋቸውን ከፍ በማድረግ ተገቢ ያልሆነ ብዙ ትርፍ እንዳያተርፉ ምርቶችን ለመጥፎ እንዳይጠቀሙ ነው፤ የዋጋ ዉሰና መብት እንዲቆጣጠር የተሰጠው: ኃላፊነት ላለው ሚኒስተር ነው፤ ዋጋቸው በቁጥጥር ከሆኑት ምርቶቹ መካከል ዳቦ፣ ወተት፣ እንቁላልና የመሳሰለሉት ይገኙበታል፡፡

በሆነ ሁኔታ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ምርቶችም ለተወሰነ ጊዜ ዋጋቸው በቁጥጥር የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ ለምሳሌ በኢራቁ ጦርነት ጊዜ በሚሳይል ጥቃት ይደርሳል ተብሎ በተፈራበት ጊዜ የወረቀት ማጣበቂያ (ፕላስተር) ላይ የዋጋ ቁጥጥር ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ዋጋቸው በቁጥጥር የሆኑ ምርቶችን በማስታወቂያ የማስታወቅ ግዴታ አለ፤ ነጋዴ በሱቁ ለሚገኙ ተስፈላጊ ጠቅላላ ምርቶች ዝርዝርና ዋጋቸውንም በምርቶች ላይ በመለጠፍ ማሳየት አለበት፤ በርቀት በሚገዙ ምርቶችም ላይ ሻጩ ግልፃዊነት ማሳየት አለበት፤ እንዲሁም በቁጥጥር ለሆነ አስፈላጊ ምርት አምራች በአስፈላጊ ምርቶች እሽግ ላይ በመንግሥት የዋጋ ቁጥጥር ውስጥ መሆናቸውን በጽሁፍ ማሳተም ይኖርበታል፡፡

# ገቢያን ማፍረስ

ሸማቹ በተገቢው መንገድ የገዛውን ምርት የማፍረስ መብቱን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ምርቱ ተስማሚ ቢሆን ወይም ጉድለት ባይገኝበትም በማንኛውም ምክንያት ሸማቹ ገቢያውን ማፍረስ ሲቻል: ሁለተኛው ደግሞ ሸማቹ ገቢያውን ማፍረስ የሚችለው ምርቱ ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም ጉድለት ሲገኝበት ብቻ ነዉ፡፡

## ምርቱ ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም ጉድለት ሳይገኝበት ገበያን የማፍረስ መብት

ወደፊት እንደተብራራው ሸማች የገዛውን ምርት ወይም አገልግሎት በሆነ ምክንያት አፍርሶ የከፈለውን ገንዘብ መልሶ ለመቀበል የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው:-

1. የገዛው ዕቃ ዋጋ ከ50 ሽኬል በላይ ከሆነ፡፡

2. ሸማቹ የገዛውን ዕቃ መመለስ አለበት:: ሸማቹ ዕቃውን በገዛበት ሱቅ ወይም ቅርንጫፎች ወይም መሸጫ ቦታዎች ለሸጠለት መመለስ ይችላል፡፡ የገዛበት ቦታ ወይም ቅርንጫፉ የባለድርሻ እንጂ በሻጩ የማይካሄድ ከሆነ፣ ለዚህም ማስመለስ እንደማይቻል በጉልህ በቀላሉ በሚታይ ቦታ በጽሁፍ ሻጭ ካስቀመጠ ዕቃውን እዚያ መመለስ አይቻለም፡፡

3. ምርቱ በተገዛበት ማሸጊያ እንደታሸገ ከተመለሰ እንዳልተጠቀመበት ለሻጩ በቂ መረጃ ነዉ፤ ገቢያው አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዘ ከሆነና ገዢው ተጨማሪ ምርት እንዲገዛ ከተገደደ(ለምሳሌ የቴሌቪዥን ጣቢያን ለመሳብ የሚረዳ ዕቃ-ማሚር) ገዢው ቢጠቀምበትም ጉዳት እስካልደረሰበት ድረስ የመመለስ መብት አለው፡፡

4. ገቢያ ማፋረሱ በህግ በተወሰነት ጊዜ መሆን አለበት፡፡

5. ገቢያ ማፋረሱ በህግ በተወሰነዉ የአፍራሽ ክፍያ: ወደፊት እንደሚብራራው መከፈል አለበት፡፡

## በማንኛውም ምክንያት ገበያን መሠረዝ የምንችላቸው  ምርቶች ወይም አገልግሎቶችና ጊዜ ገደቦች:

### የምርቱ/የአገልግሎቱ  ዓይነት

የቤት ዕቃዎች፣ ያልታሸጉ የቤትና የጓሮ ዕቃዎች፣ ያልታሸጉ የምግብ እቃወች ዉጭ፣ ስዓቶች፣ የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችና የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች: የማገናኛ መሳሪያዎችም፣ የውኃ ማጣሪያና የተፈጥሮ ውኃ(ሜኔራል ዉሃ) መያዣዎች

ምርቶች ወይም ዕቃዎች ከመጀመሪያ እሽጋቸው ያልወጡ በገዢው ያልተከፈቱ፣ ገዢው ገዝቶ ገና ያልተቀበላቸዉ ዕቃዎች ተሽጠው ስላለቁ ገና መሰራት ወይም ማስመጣት ስላለባቸዉ፣ በሸማች ልዩ ትዛዝ ወይም መለኪያ ያልተዘጋጁ።

አልባሳትና ጫማ

የማስተናገጃ አገልግሎት፣ መጓጓዣ፣ እረፍትና መዝናኛ። ነገር ግን ከእስራኤል ክልል ውጭ ሙሉ በሙሉ ሚከናዎን አገልግሎት ካልሆነ (ከእስራኤል የጀመረና በሌላ አገር አየር መንገድ የሚቀጥል በረራ)፣ ከእስራኤል ክልል ውጭ የሚከናወን የአንድነት የዕረፍት ጊዜ ይህ አንቀጽ አይሸፍነዉም። ከእስራኤል ዉጭ የሚከናወኑ አገልግለቶች የመሠረዝ መብት የሚነፈገዉ፤ አዘጋጁ: አስቀድሞ ለሸማች: ከዉጭ አገር ያለዉ ባለሙያ: ገብያ የሚሰረዝበትን ሁኔታ ካሳወቀ ነዉ። ይህ ሃላፊነት በሻጭዉ ላይ ይሆናል፡፡

ኩርስና ትምህርቶች "ኩርስ" በፐሲኾሜትሪ ተቋማት ቁጥጥር ህግ ዉስጥ ካልሆነ በስተቀር።

የመዋቢያና የውበት አገልግሎት ፀጉርን የመንቀል አገልግሎት ጭምር፣ ለረዥም ጊዜ ዕረፍት ስምምነት ማለትም በክፍያ ከዓመት በላይ የሚደረግ ስምምነት፣ ሸማች፣ ለከፈለበት ክፍያ የአልጋ ቅናሽና መሻሻል የሚአስገኝለት፤ ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ቢኖረዉም: ለምሳሌ ጉዞን የሚአጠቃልል ቢሆንም ባዩሆንም: አቫልነት ወይም የክበብ ቅናሽ ክፍያ በቴሌኮሚኬሽን ህግ እንደተገለፀው ፈቃድ ባለው በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ አገልግሎት ሰጪ አገልግሎት አቫል፤ በተንቀሳቃሽ ስልክ ዘዴ በአንቀፅ 2(ሀ4) መሠረት በሬዲዮ በእጅ ስልክ መመሪያ ለሚሰጡ አገልግሎቶች፣ ልዩ ፈቃድ ባለው ወይም በቴሌኮሚኬሽን ህግ ሀ-4ሽ4 መሠረት የኢንተርኔት መግቢያ አጠቃላይ ባለፈቃድ የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ በሰውነት ማዳበሪያ(ጂም) ክለብ ወይም የጤና ክለብ(ስፓ)፣ በመተዋወቂያ ወይም በመተጫጫ ክለቦች፣ የሎተሪና የቁማር መጫወቻ ክለብ አባል መሆን፡፡

በክስተት የሚሸጡ ንብረቶችና አገልግለቶች በስጦታና በእጣ ዕድል አቫብሎ  አገልግሎቶችን ለማሳወቅ፡፡

ተሽከርካሪ ማለት በእስራኤል የትራንስፖርት ህግ ደምብ ገለፃ ከአስመጪ የተገዛ አዲስ ተሽከርካሪ፡፡

ከ3,000 ሸኬል ያልበለጠ ዋጋ የተከፈለበት ጌጣጌጥ፡፡

## የመሠረዣ ጊዜና ሌሎች ክልከላዎች ካሉ

በዚህ ጉዳይ ዕቃውን ከተቀበሉበት በ14 ቀናት ውስጥ በሌላ መንገድ ካልተረጋገጠ በቀር የዕቃውን እሽግ መክፈት ብቻውን ዕቃውን እንደመጠቀም ወይም እንደመደብዘዝ አይቆጠርም፡፡ ከኤሌክትሪክ፣ ከጋዝ ወይም ከውኃ ጋር ማያያዝ ዕቃውን እንደመጠቀም ያስቆጥራል፡፡

ዕቃውን ከተረከቡበት በ14 ቀናት ውስጥ፡፡

ዋጋውን የሚያሳየው እስካልወረደ ድረስ ዕቃው ከተገዛበት እስከ ተከታዮች 2 የረፍት  ቀናት ያልሆኑ መጨረሻ ቀናት፡፡

ውል ከተፈረመበት 14 ቀናት ውስጥና ሥረዛው አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ የዕረፍት ቀናት ባልሆኑ በ14 ቀናት መሆን ይኖርበታል፡፡

ግዢው ከተከናወነ በ14 ቀናት ውስጥና አገልግሎቱ ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ የዕረፍት ቀናት ባልሆኑ በ7 ቀናት መሆን ይኖርበታል፡፡

ግዢው ከተከናወነበት ወይም ውሉ በጽሁፍ ወይም በህጉ የተደነገጉትን ነጥቦች የያዘ የጽሁፍ መረጃ ከተሰጠበት በ14 ቀናት ውስጥ አገልግሎት መሰጠት በመጀመሩና ባለመጀመሩ መካከል ወይም ግብብይቱ ለተወሰነ ጊዜ  ቢሆንም፡፡

ዕቃን ለመግዛት፣ ዕቃን ከተቀበሉበት በ14 ቀናት ውስጥ። አገልግሎት ለመግዛት ለአገልግሎቱ ከተስማሙበት በ14 ቀናት ውስጥ ወይም በጽሁፍ ውል ወዱም በጽሁፍ ዉል ካስረከቡበት በሸማቾች ተከላካይ ህግ አንቀፅ ሐ_13 መሠረት ውሉ በጽሁፍ ወይም በህጉ የተደነገጉትን ነጥቦች በያዘ የጽሁፍ መረጃ ከተሰጠበት በ14 ቀናት ውስጥ ወይም ዘግይቶ በሚደርሰው አገልግሎት መስጠት ቢጀመርም ባይጀመርም ግብይቱ ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም፤ ለረዘም ጊዜ ላልሆነ ግብይት ሸማቾችን በሚከላከል ህግ አንቀፅ ኀ13 እንደተገለጸው፣ ገቢያው ከተከናወነበት እስከ ተከታዮች 2 የዕረፍት ቀናት ያልሆኑ መጨረሻ ቀናት አገልግሎቱ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ፡፡

ገቢያው በተከናወነበት በ14 ቀናት ውስጥ :በእስራኤል የትራንስፖርት ህግ ደምብ  በገዡ ስም ከመመዝገቡ በፊት፡፡

ዕቃው ከተገዛበት እስከ ተከታዮች 2 የዕረፍት ቀናት ያልሆኑ ቀናት፡፡

## የመሠረዝ መብት የማይከናወንባቸው ልዩ ሁኔታዎች

### መሠረዝ የማይቻልባቸው፡

የቤት ዕቃ በቤት ውስጥ ከተገጣጠመ፣ በተለይ ለዕቃ ገዢው ተብለው በልክ የተሠሩ ዕቃዎች፣ በዕቃ ገዢው ልዩ ትዕዛዝ የተሠሩ፣ እንደ ህጉ ተመላሽ የማይሆኑ ዕቃዎች፣ የምግብ ምርቶች፣ መድኃኒቶችና ተጨማሪ ምግቦች፣ የሚፈጁ እቃዎች: መረጃ ማለት በኮምፒዩተር ህግ እንደተገለጸዉ፣ ጋዝ፣ ለመቅዳት ለመገልበጥ ወይም ለማባዛት የሚቻሉ ንብረቶች ገዢው እሽጋቸውን ከከፈተ፣ የውኃ መዋኛ ልብስን ጨምሮ የውስጥ አልባሳት፣ ከስዓቶች በቀር ከ3,000 ሸኬል በላይ የተከፈለባቸው ጌጣጌጦች፣ እቃ የሚቀበልበት ቀን ካለፈ ከተገበያዩበት ከስድስት ወራት በኋላ እንዲደርሱለት ለጠየቀ ዕቃ ገዢ፣ በኩፖን የተከፈለባቸው ዕቃዎች፣ በስጦታ ካርድ ወይም በሚሞላ ካርድ መግዛት፣ የመስተናገጃ አገልግሎት፣ ጉዞ፣ ዕረፍት ወይም መዝናናት፣ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ከእስራኤል ውጭ ለመሆን የታቀደ ለምሳሌ ከእስራኤል የወጣ በረራና ቀጣዩ በሌላ አገር አየር መንገድ ወይም ከእስራኤል ውጭ መዝናናትና ዕረፍት ከእስራኤል ውጭ በረራ ከዚያም ወደ እስራኤል መመለሻ በረራ ካልሆነ በቀር፣ ይህም: ጊዜ አገልግሎት ሰጪው ከእስራኤል ውጭ የአገልግሎት አቅራቢ የመሠረዝ ደምብ ካስረዳ ነዉ፡፡

## ለተሠረዘ ገቢያ የተከፈለውን ገንዘብ ማስመለስ

ገቢያው እንደ ህጉ ከተሠረዘ ሻጩ የተከፈለውን ለገዢው መመለስ አለበት፡፡ ዕቃ ገዢው ከሻጩ መግዛቱን በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት:፡ ለዚህ የደረሰኝ፣ የታተመ ወረቀትና የመለወጫ ወረቀቱን በማሳየት ወይም ሌላ ማስረጃ እንደ የክፍያውን መጠንና ጊዜውንና በምን እንደከፈለ በማሳየት ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ ሻጩ በተቻለው መጠን ገቢያው በተሰረዘበት ቀን ገንዘቡን መመለስ ይኖርበታል፡፡ ቢበዛም ከተገዛበት 7 የሥራ ቀናት ሳያልፉ ክፍያውን መመለስ አለበት፡፡

ክፍያው በተከፈለበት ዓይነትና መንገድ ተመላሽ ይሆናል፡፡

**ክፍያው በጥሬ ብር ከነበረ -** ማለሳዉ በጥሬ ብር ወይም ወዲያው ሊከፈልበት በሚቻል ቸክ ይመለሳል፡፡

**ክፍያው በቸክ ከነበረ -** ቸኩ በተዘረዘረ በ5 ቀናት ውስጥ በካሽ ወይም ወዲያው ሊከፈልበት በሚችል ቸክ ተመላሽ ይሆናል፤

**ክፍያው በብድር ካርድ (ክሬዲት ካርድ) ከነበረ -** ሻጪ የክፍያ ትዛዙን ይሠርዛል፤ ክፍያው ወደ ሻጩ ገቢ ከሆነ ክፍያው በጥሬ ብር ወይም ወዲያው ሊከፈልበት በሚችል ቸክ ይመለሳል። የክሬዲት ካርድ ኮምፓኒ ክፍያውን መቀበል የሚችል ከሆነ ክፍያዉን ወደ ሸማቸ ክሬዲት ካርድ በቀጥታ: ወዲያውኑ: ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

## ገቢያን ለማፍረስ የሚከፈል ክፍያና ሌላም : ሻጩ ለገዢው ከሚመለሰው ምን የመቀነስ መብት አለው?

ከሚከተሉት ልዩ ሁኔታዎች በቀር ሻጩ ከገዢው ክፍያ ምንም ማስቀረት የለበትም፡፡

ሀ. የመሠረዣ ክፍያ፡ 5% ወይም ከዕቃው ወይም ከአገልግሎቱ ዋጋ ወይም 100 ሸኬል ከሁለቱ ዝቅተኛው፡፡

ለ. የመግጠሚያ ክፍያ፤ ለአገልግሎት መስጫ የሚሆነው ዕቃ ከተገጣጠመ 100 ሸኬል(ባለፈው አንቀፅ እንደተገለጸው ለመሠረዝ ከሚከፈለው በተጨማሪ)

ሐ. የካርዱን ወጪ ለመላቀቅ፣ ግብይቱ በዱቤ ካርድ ከተከናወነ ሻጩ ለክሬዲት ካርድ ኮምፓኒ የአገልግሎት ክፍያ ወጭ ማዉጣቱን ካረጋገጠ።

መ. ግብይቱ አገልግሎት ከሆነ ጥቅም በተደረገበት አንፃር ገዢው መክፈል ይኖርበታል፡፡

## በስጦታ የተቀበሉትን የመሠረዝ መብት

ዕቃ ገዢው ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ከነጋዴው ባይገዛም በተዘዋዋሪ ከሌላ በስጦታ መልክ ቢቀበልም (ስጦታው የመግዣ ሠነድ ቢሆንም: ግን የሥጦታ ካርድ ካልሆነ) የመሠረዝ መብት እንዳለው ህጉ ወስኗል፡፡

በዚህ ሁኔታ ለመሠረዝ የመለወጫ ካርዱን ወይም የገዛበትን ሌላ ማረጋገጫ፣ የተገዛበትን ጊዜ፣ የከፈለውን የገንዘብ መጠንና በምን እንደከፈለ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

ለሥጦታው የተከፈለው በጥሬ ብር ከሆነ: ምለሳዉ በጥሬ ብር ወይም ወዲያው በሚመነዘር ቸክ ይመለሳል። ሥጦታው በተመነዘረ ቸክ ተከፍሎ ከሆነ በካሽ ወይም ወዲያው በሚመነዘር ቸክ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ይመለሳል። ክፍያው ገና ባልተመነዘረ ቸክ ተከፍሎ ከሆነ የሚመለሰው ክፍያ ቸኩ ከሚመነዘርበት በ5 ቀን ውስጥ ይከፈላል፡፡ የስጦታዉ ዋጋ በክሬዲት ካርድ ተከፍሎ ከሆነ መልሱ በጥሬ ብር ይሆናል: ይህም ስጦታዉን የገዛዉ ዋጋዉን ከከፈለ ነዉ፡፡

## በርቀት  የተከናወኑ ግብይቶች ስረዛ

በርቀት የሚከናወን ግብይት ሻጬና ገዢው ፊት ለፊት የማይገናኙበት የግብይይነት ዓይነት ነው:: እንዲህ ዓይነት ገቢያ ሊከናወን የሚችለው በስልክ፣ በኢንተርኔት፣ በፖስታ፣ በፋክስና በመሳሰሉት አማካይነት ነው፡፡ በርቀት ከሚደረግ ግዢ ስለሻጩ፣ ስለዕቃው፣ ስለዋጋውና ስለመክፈያ ዘዴው፣ ዕቃው መቼና በምን መንገድ እንደሚደርስ የግብይት ሁኔታዉ እስከመቼ እንደሚቆይና ስለዕቃው የሚሰጥ ኃላፊነት ካርድ ግልፅ መሆን እንዳለበት ህጉ በሻጩ  ላይ ሃላፊነት ይጥላል፤ በተጨማሪም ሻጩ ለገዢው ዕቃው ከመድረሱ ሳይዘገይ ህጉ በሚጠይቀው መጠን፣ ህጉ በሚያዘው ስለገቢያው ዝርዝር መግለጫ፣ ዕቃ ገዢው ገቢያውን የመሠረዝ መብቱን የሚጠቅስ መረጃ የያዘ  ለገዢው መላክ ይኖርበታል፡፡

በርቀት የተገዛን ዕቃ ያለምንም ምክንያት ገዢው በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረዝ ይችላል:

- ገዢው ዕቃውን በተቀበለበት ወይም ከላይ እንደተገለፀው የመግለጫ መረጃ ከተቀበለበት ጀምሮ በ14 ቀን ውስጥ ገዢው እንደሚሥርዝ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
- ገዢው ግዢን እንደሚሠርዝ ለሻጩ በጽሁፍ በፋክስ፣ በፖስታ ወይም በኢጦማር(ኢ-ሜል) ማሳወቅ\መላክ ይኖርበታል፡፡
- ከሠረዘ በኋላ ገዢው የተቀበለውን ዕቃ ለሻጩ መመለስ አለበት፡፡
- ግብይቱ ለረዥም ጊዜ የማይቀጥል አገልግሎት መስጠት ከሆነ ገዢው ገብያውን ከገዛበት ቀን  በ14 ቀን ውስጥ እንደሚሠረዝ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን አገልግሎቱ ከመጀመሩ 2 ቀን በፊት መሆን አለበት።
- ለረጅም ጊዜ ለሚቀጥል አገልግሎት ከሆነ ግብይቱ በተፈጸመበት ወይም የገቢያውን ምንነት የሚገልጸው ጽሁፍ ከደረሰበት ከሁለቱ ዘግይቶ ከደረሰው በ14 ቀን ውስጥ ይህም አገልግሎት መስጠት ቢጀመረም ባይጀመርም፡፡
- በርቀት የሚከናወኑ የምግብ ነክ ገብያን፣ ሊበላሹ ለሚችሉ ዕቃዎች(ለምሳሌ አበባ)፣ በተለይ ለገዢው ተብለው የተመረቱ ምርቶች፣ ለመቅዳት ለመገልበጥ ወይም ለማባዛት የሚቻሉ ዕቃዎች ገዢው እሽጋቸውን ከከፈተ በህጉ መመለስ የሌለባቸው ዕቃዎችና ሌሎች: የስረዛዉ ባለስልጣን ሚኒስቴር እንደመመሪያው የማይመለሱ በፓርላሜንቱ የገንዘብ ኮሚቴ ያጸደቃቸው መምሪያዎች።
- በርቀት ለሚደረጉ የመዝናናትና የጉዞ ገብያዎች የስረዛዉ ቀን ከአገልግሎት የምስጫዉ ቀን በ7 የሥራ ቀን በፊት ካልሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡

በርቀት የተገዛን ዕቃ: ገዡ: በፍላጎቱ እንጂ በዕቃዉ ጉድለት ወይም የማይስማማ ሆኖ ሳይሆን የሰረዘዉ: ገዢውን ቢሠርዝ 100 ሽኬል ወይም ከዋጋው 5% ከሁለቱ ዝቅተኛውን ለመሠረዣ ክፍያ ሻጩ ገዢውን ማስከፈል ይችላል፡፡ ገዢው የሠረዘው ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በጊዜው ባለመድረሱ ከሆነ: ከገዡ የደረሰዉ ምርት ወይም አገልግሎት ከምርቱ ወይም ከአገልግሎቱ መግለጫ ጋር ካልተስማማ የግዥ መሰረዣ ማስከፈል አይቻልም።

ግብያዉ በሚሰረዝበት ጊዜ: ሻጭ: ወደ ክሬዲት ካርድ ኮምፓኒ የሰደደዉን የግብያ ማፍረሻ መልክት ግልባጭ መስጠት ግዴታዉ ነዉ።

ገዢው ዕቃ ግዥውን ቢሠርዝ የገዛውን ዕቃ ጉዳት ሳያደርስ መመለስ እንዳለበት ማስታወስ አለበት፤ የዕቃው ሁኔታ ከይዘቱ በጣም ቀንሶ ከተገኘ ሻጩ ገዥውን ስላደረሰው ጉዳት መክሰስ ይችላል፡፡ ስለዚህ ገቢያን ለመሠረዝ ከወሰናችሁ: በህግ ደምብም ቢሆን ዕቃውን ከመጠቀም ተጠበቁ፡፡ ነገር ግን እሽጉ መክፈት እንደ ጉዳት አይታሰብም። ይህም በህግ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች እንደ ማባዛትና ለመቅዳት የሚሆኑ ዕቃዎች፣ የምግብ ምርቶች  በልዩ ትዕዛዝ የተዘጋጁ ዕቃዎች ካልሆነ በስተቀር።

ለረጂም ጊዜ ለሚሰጡ አገልግሎቶች አገልግሎቱ ከተጀመረ በኋላ ለተሠረዘ ገብያ  ለተጠቀመበት አገልግሎት  ገዢው ለሻጩ በአንፃሩ ይከፍላል። ሻጭ ከገዢው ቤት: ዕቃውን  በልዩ ሁኔታ ተክሎ ከሆነ(ለምሳሌ ክባሊም ወይም በላቪያን የሚያሳዩ ዕቃዎች) ሻጩ ከመሠረዣው ክፍያ በተጨማሪ የመትከያ ወጩን እስከ 100 ሽኬል ማስከፈል ይችላል፡፡

## የሽቀጥ ገበያን ማፍረስ

የሽቀጥ ገበያ : በግፊት የሚደረግ ገቢያ ሻጩ በተለመደ ንግድ ቤት ሳይሆን በየትም ቦታ ገዢውን በመጠየቅ የሚደረግ ገቢያ ነው። ለምሳሌ ሻጩ ከዕቃ ገዢው ቤት፣ ሥራ ቦታ፣ በመሚማርበት ቦታ ወይም አካባቢ፣ ድረስ በመምጣትና እንዲሁም በገቢያ አዳራሽ(ሞል) በማዕከላዊ የአብቶቡስ ጣቢያዎችና በመሳሰሉት ቦታዎች የሚደረግ መገበያየት ወዘተ።

በሽቀጥ የተደረገን ገበያ በማንኛውም ምክንያት ምርቱን በገዛበት ወይም በተቀበለት በ14 ቀናት ውስጥ ለሻጩ መልዕክት በመላክ ማፍረስ ይችላል፡፡ አገልግሎትን የተመለከተ ከሆነ የተገበያየበትን ስምምነት ከፈረመበት ወይም ህጉ በወሰነው ስለአገልግሎቱ ምንነት የሚገልፀውን የጽሁፍ መረጃ ከተቀበለበት: ከሁለቱ ዘግይቶ በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ: አገልግሎቱን መቀበል ቢጀመርም ገዢው ማፍረስ ይችላል፤ በግፊት\በሽቀጥ ስለተደረገው ግብይት ገዢው ቢያፈርስ የማፍረሻ ክፍያ መክፈል የለበትም፡፡

አገልግሎት መስጠት ከተጀመረ በኋላ ከሆነ ሸማች ገብያዉን ያፈረሰው የተጠቀመበትን አንፃራዊ  ክፍያን ለሻጩ ይከፍላል።

ሻጭ በሸማች ቤት  አገልግሎቱን ለመጠቀም የሚያስችል ልዩ አገጣጠም ካደረገ (ለምሳሌ በቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ለማየት የሚያስችል መሣሪያ ክባሊም ወይም በላቪያን የሚያሳዩ ዕቃዎች የመሳሰሉ) ሻጩ ለመተከያ ወጭ እስከ100 ሽኬል ማስከፈል ይችላል።

# የጊዜ ገደብ ላላቸው የተወሰኑ ገቢያዎች ልዩ መመሪያዎች

በግዜ የተገደበ ገቢያ ማለት ገዢው ረዘም ላለ ጊዜ የሚቀጥል አገልግሎት የሚገዛበት ግብይት ነው፤ ለምሳሌ ለውኃ መዋኛ ወይም ለሰውነት ማዳበሪያ(ጂም) ደንበኛ መሆን:: እኒህ ዓይነቶችን ግብይቶች ከመደበኛው የማፍረስ መንገድ የተለዩ ተጨማሪ መንገዶች አሉ:: ለምሳሌ ደንበኛው አገልግሎቱን መጠቀም ከጀመረ በኋላ መጨረሻው ላይ ሳይደርስ መሠረዝ ይችላል፡፡ ዛሬ ለተወሰነ ጊዜ ገቢያ ህጉ በሁለት ዓይነት ይሠራል-በመዝናኛ ቦታና በሰውነት ማዳበሪያ(ጂም) ተቋማት ይሠራል፡፡

## የመናፈሻ ቦታዎች

1. **የመናፈሻ ቦታ ምንድን ነው?**

   የመናፈሻ ቦታ ማለት በክፍል ወይም መኖሪያ ቤት ለቀጣይ ጊዜያት ቢያንሰ ለሦስት ዓመትና ቢያንሰ በዓመት ሁለት ቀናት የመኖሪያ ቦታ የመጠቀም መብት ነው፡፡

2. **መልዕክት የመላክ ግዴታ**

   ሸማች ለሻጭ የጽሁፍ መልዕክት በአደራ ደብዳቤ: በኢ-ጦማር ወይም በፋክስ መላክ አለበት፡፡

3. **መሠረዙ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ**

   ተጠቃሚው ከሰደደዉ መልእክት: በሁዋላ: በቅርቡ የሚገኘዉ በመዝናኛዉ የመጠቀም መብት ሲደመደም:: በዓመታው የዕረፍት ጊዜ መጠቀም ጊዜ የተላከ መልዕክት: የዚያኑ ዓመት አገልግሎት ሲደመደም ይሆናል::

4. **ክፍያዎች**

   ሻጭ ገዢን ሊአስከፍል የሚችለዉ በሚመጣዉ የተጠቀሱትን ብቻ ነዉ፡

   ሀ. መሠረዙ ተግባራዊ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ በመዝናኛው የተጠቀመበትን አንፃራዊ ክፍያ ::

   ለ. ከ24.3.2014 ጀምሮ ከተገዙ የመናፈሻዎች ቦታዎች ብቻ መናፈሻውን ከመግዛቱ በፊት ሻጩ ለገዢው ሲገበያይ ባሳየው ግልፅ መረጃ ዋጋ ላይ በአንቀፅ ሀ የተጠቀሰው ክፍያ ከተነሳ በኋላ 50%- ይህም ሻጩ የገዥን ለሌላ የመሸጥ መብቱን አይከለክለውም፡፡

   ሻጩ ምንም የመሠረዣ ክፍያ ከደንበኛው መጠየቅ የለበትም፤ እንዲያውም ደንበኟዉ የከፈለውን ከነወለዱ ጨምሮ በአንቀፅ 4 መሠረት ማስከፈል የሚገባዉን ካወረደ በሁዋላ መመለስ አለበት፡፡

# የሰውነት ማዳበሪያ (ጂም) ተቋማት

የሚከተሉት መመሪያዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ከ24/3/14 ለተከናወኑ ግብይቶች ነው፡፡

**የሰውነት ማዳበሪያ ተብሎ <u>የሚታሰበው</u> ምንድን ነው?**

ጡንቻን በሚያጠነክሩ መሣሪያዎች ሰውነትን በአካላዊ ጥረት ማለማመድ የሚቻልበት ቦታ፤ እንደ ውኃ መዋኛ፣ የስፖርት ልምምድና ሰውነትን ማስተካከል ሳውናና ጃኩዚ ያለበት ማንኛውም የስፖርት ወይም የጤና ክለብ መለማመጃ ቦታ ሁሉ።

**የሰውነት ማጠናከሪያ ተቋም ተብሎ <u>የማይታሰብ</u> ምንድን ነው?**

በምዝገባ ሊቀላቀሉበት የሚቻል ዘግይቶ ሊቀላቀሉበት የማይቻል የትምርት ፕሮገራም ነው፤ በዓመት እስከ አምስት ወር የሚሠራ የውኃ ዋና አገልግሎት <u>ብቻ</u> የሚሰጥበት ቦታ።

በሰውነት ማጠናከሪያ ቦታ: ገደብ ያለዉ ውልን ለማፍረስ መልዕክት መላክ የግድ ነው፤ መልዕክቱ በጽሁፍ ሆኖ በአደራ ደብዳቤ፣ በኢጦማር ወይም በፋክስ መላክ ይኖርበታል፡፡

መልዕክቱ ከተላከበት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መሠረዙ ተግባራዊ ይሆናል።

ሻጩ ገዥን የስረዛ ገንዘብ ማስከፈል የሚችለዉ: አገልግሎት ስጦታዉ ከተጀመረ ነዉ።በሚቀጥሉት የተገደበ ነዉ:

አንፃራዊ ክፍያ - የዉሉ ስራዥ ተግባራዊ እስኪሆን ያለፈዉ ያገልግሎት መብት

የማሠረዣ ክፍያ – ለገገርው ከግብይቱ በፊት የጊዜ ገደብ ለሌለው ጊዜ ወርሃዊ ክፍያውን በጽሁፍ ሻጩ ካስታወቀ ብቻ።

የስረዛ ክፍያው: ከታች በተገለፁት 3 ምርጫዎች: ዝቅተኛዉ ይሆናል።

1. የማሠረዣ ክፍያ የሚታሰበው ደንበኛው ተጠቃሚ ሆኖ የቆየባቸው ወራት በወርሃዊ ክፍያውና በአማራጩ ወርሃዊ ክፍያ መካከል ባለው የዋጋ ልዩነት <u>ተባዝቶ</u>
2. ደንበኛው ለገዛው መክፈል ከነበረበት ማንኛውም ዋጋ ከመቶ እጅ (የመመዝገቢያ ክፍያን ጨምሮ) በሚከተሉት መጠን ይሆናል፡

   25 እጅ ከመቶ - ገብያው ከተወሰነለት ጊዜ በአንድ ሦስተኛው ጊዜ ውስጥ ከተሠረዘ

   20 እጅ ከመቶ - ገብያው ከተወሰነለት ጊዜ በሁለት ሦስተኛው ጊዜ ውስጥ ከተሠረዘ

   17 እጅ ከመቶ - ገብያው ከተወሰነለት በመጨረሻው በአንድ ሦስተኛው ጊዜ ውስጥ ከተሠረዘ
3. ገብያው ከተቋረጠበት ጊዜ እስከ ፍጻሜው ድረስ ገገርው ለአገልግሎቶ መክፈል የነበረበት የክፍያ መጠን፡፡

## ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም በጉድለት ምክንያት ገቢያን ማፈርስ

የገዛውን ዕቃ ሁሉ የመፈተሽ የገዥ ኃላፊነት ነው። ሻጩ ደግሞ ዕቃዎች ደኅና መሆናቸውን ገዢው እንዲፈትሽ ዕድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

ተስማሚ ባለመሆኑ ወይም ጉድለት ከተገኘበት ገዢው ወዲያውኑ ለሻጩ ማሳወቅ አለበት። ተስማሚ አለመሆኑ ወይም ጉድለቱ ግልፅ ከሆነ ዕቃ ገዢው በጊዜው ካላሳወቀ ዕቃ ገዢው በእኒህ ምልክቶች ሊተማመን አይችልም፡፡ የዕቃው ተስማሚ አለመሆንና ጉድለቱ ድብቅ ከሆነ ጉድለቱ እንደታወቀ ለሻጩ ማሳወቅ አለበት፡፡

# ኃላፊነትና አገልግሎት

## ኃላፊነት

ሻጩ ለገዢው የዋስትና\የኃላፊነት ካርድ መስጠት ይኖርበታል: በዚህም: ኤሌክትሪክ ዕቃዎች፣ ኤሌክትሮኒክስና የአዲስ ጋዝ ዋጋቸው ከ150 ሸኬል በላይ የሆኑ፡፡

በሚሰጡ የዋስትና ካርዶች መጠቀስ ካለባቸው መካከል ኃላፊነቱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣አገልግሎት ሰጪዎች የገገርን ጥሪት መቀበል ያለባቸዉ ወደብ ግዜዎች: አገልግሎት ሰጪዎች ወደ ገዢው ቤት እስኪመጡ ገዢው መጠበቅ ስላለበት ጊዜና ሻጩ መቀያየሪያ ዕቃ ስለመኖሩ በተሰጡ አዋጆች ተወስኗል፡፡

ለገዢው ከተሰጡበት ወይም ምርቱ በቤቱ ከተገጠመበት ጊዜ አንስቶ: ከሁለቱ ዘግይቶ ከደረሰው: ለአንድ ዓመት የዋስትና መሰጠት ያለባቸው የዕቃ ዝርዝሮች አሉ። እንዲሁም ከሽያጭ በኋላ ስለሚሰጥ አገልግሎት መስፈርት: በኤሌክትሪክ ዕቃዎች፣ ኤሌክትሮኒክስና የአዲስ ጋዝ ዋጋቸው ከ150 ሸኬል በላይ የሆኑ መመሪያው ወስኗል፡፡ በዚህ መመሪያዎች አምራቹ ለሚመለከታቸው ምርቶች ለተወሰኑ ጊዜያት መለወጫ ዕቃዎችን መስጠት እንዳለበት ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁም በኢየሩሳሌም፣ በቴል አቪቭ፣ በሐይፋና በብኤር ሸቫ ወይም በቅርብ አካባቢው የአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች መቋቋም የግድ ሲሆን በተወሰኑ ጊዜያት ጥገና ማድረግ ይገባል። እኒህን ምርቶች በተመለከተ: ምርቶች: ቢያንስ: የሚከተሉትን ነጥቦች የያዙ የዋስትና ማጣበቂያዎች ጨምረው መያዝ እንዳለባቸው ተወስኗል፤ አገልግሎት ለመቀበል ዕቃ ገዢው መረጃ እንዳያሳይ ሙሉ ዋስትናውና ለተወሰነ ጊዜ የዋስትና ካርድ-ካለ የሚያበቃበት ጊዜ፡፡ በዋስትና ማጣበቂያ ፋንታ፣ ዕቃ ሻጪው በተከታታይ ቁጥሮች ወይም ልዩ የመለያ ቁጥር ዕቃ ገዢው በዕቃው ልዩ ቁጥር ወይም ልዩ መለያ ማጣራት እንዲችል፣ በኢንተርኔት፣ በነፃ የስልክ አገልግሎት ወይም የዋስትና ካርዱ የሚያበቃበትን እንዲያውቅ ዘንድ ሻጩ ለዕቃ ገዢው ዕድል መስጠት ይኖርበታል፡፡ ገዢው ጊዜው ሲደርስ የዋስትና ካርድ የማይጠየቅ ከሆነ።

እንዲሁም የቤት ዕቃዎችን እንደ ፍሪጂደር፣ የልብስ ማጠቢያ ማሽን፣ ፍሪዘር፣ የጋዝ ወይም የኤሌክትሪት ምድጃ፣ የአየር ማቀዝቀዣ፣ የምግብ መሥሪያ ምድጃዎች፣ መጠናቸው ከ21 ኢንች የበለጡ ቴሌቪዥን፣ የዕቃ ማጠቢያ ማሽን፣ የልብስ ማድረቂያዎች የቤት ዕቃዎችን ለመጠገን በተወሰነ ግዚያቶች ፤ እነዚህ በዕቃ ገዢው መኖሪያ ቤት ይከናወናሉ፡፡

ጥገና ጥሪው ለቴክኒሺያኑ ደርሶ ለጥገና ለተቀጠረዉ ሰአት በዛ ቢባል እስከ 2 ስዓት መዘግየት ይችላል፤ ከዚህ በላይ ጊዜ ከዘገየ ወይም ያለበቂ ምክንያት መምጣቱን ቢሠርዝ ለደንበኛው ተገቢ ካሣ ይገባዋል፡፡

ዕቃ ገዢ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት ቢያስብ ለዕቃው የሚሰጠውን የዋስትና ካርድ አስቀድሞ ለማየት ቢጠይቅ መልካም ነው፤ በዚህ ዓይነት በዋስትናው ካርድ ምን እንደተጠቀሰና እንዳልተጠቀሰ ማወቅ ያስችለዋል፤ ይህ ደግሞ ዕቃውን ለመግዛት ወይም ላለመግዛት ለመወሰን ያስችለዋል፡፡

ዕቃዎቻቸው እንዲሸጡላቸው ነጋዴዎች ረዘም ላለ ጊዜ የሚሰጡት የዋስትናን ካርድ ልብ ልንል ይኖርብናል፤ የዋስትና ካርድ ባልተሰጠበት ዓመት ሁሉ ዕቃ የገዛው ሌላ የአገልግሎት ገንዘብ መክፈል እንዳለብን ሊታወቅ ይገባል፡፡ ስለዚህ ይህን ሁሉ ከሚገዛው ዕቃ ዋጋ ውስጥ በማስገባት በመጨረሻ ውሳኔያችን ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

ከግዢ በኋላ ለሚሰጥ የዋስትና ካርድ ሻጩ በህጉ መሠረት መስጠት እንዳለበት ማስታውስ ይገባናል፤ ህጉ ከሚያዘው በላይ ሰፋ ያለ ዋስትና ሻጩ ቢሰጥ በሰፊው ዋስትና የተጠቀሱት ነጥቦች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## ነፃ የስልክ አገልግሎት

የመገናኛ ካምፓኒዎች እንደ ኢንተርኔት፣ ሴሉላር፣ ኬብል፣ ላቪያን(ሳተላይት)፣ ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ፣ ውኃና የረዢም ጊዜ የህክምና አገልግሎት፣ ሻጩ ለሸጣቸው ጉዳት ላላቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከባለሙያዎች መልስ ለመቀበል ለገዢዎች ነፃ የስልክ አገልግሎት መስጠት አለባቸዉ ብሎ ተደንግጓል።

ስልኩ የሰዉ መልስ ተቀባይነት የሚሆነዉ ከሦስት ደቂቃ ሊአልፍ የሚችል ከሆነ: መደወል ከተጀመረ: በሁለት ደቂቃ ውስጥ: ዕቃ ገዢው መስመር ላይ ስንት ጊዜ መጠበቅ የሚኖርበትንና ደውሎ መልዕክት የሚያስቀምጥበት አማራጭ ሻጩ ሊሰጠውና በ3 ስዓትም ውስጥ ሰብአባዊ መልስ መስጠት ይገባዋል። ዕቃ ገዢው በመጨረሻ: ሁለት የሥራ ሰአቶች ዉስጥ ለሻጩ ካመለከተ: ሻጩ ቁጥሩ በሚታይ ስልክ በሚመጣዉ ሥራ ቀን ከመጀመሩ በስዎስጥ ሰአት ዉስጥ መደወል ይኖርበታል: ይህም ቴክንሽያን ካልሆነ፤ ሻጩ መልሶ ይደውልለት ዘንድ እንዲችል ይረዳዋል። ሻጩ ለዕቃ ገዢው ደውሎ ዕቃ ገዢው ባይመልስለት መልዕክት ካስቀመጠለት ጊዜ ጀምሮ ከሦስት ስዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደገና መቼ መልሶ እንደሚደውልለት የድምፅ ወይም የጽሁፍ መልዕክት ሻጩ ያስቀምጥለታል፤ ሻጩ ለዕቃ ገዢው ሁለተኛ ደውሎ ዕቃ ገዢው ባይመልስለት ዕቃ ገዢው እንደገና በአዲስ መልክ ማመልከት እንዳለበትና መልሶ እንዲደውልለት ስልክ ቁጥር ከመልዕክቱ ጋር ያስቀምጥለታል፤ አገልግሎት ወይም ምርት ለመስጠት በአካባቢው አጠቃላይ ብልሽት ከተፈጠረ ለደንበኞች አጠቃላይ ችግር ስለመኖሩና መቼ መፍትሄ እንደሚሰጥ መልዕክት እስካስተላለፈ ድረስ ሻጩ ወይም አገልግሎት ሰጪው ሰብአቢ መልስ የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡

# አንድ ዓይነት መደበኛ ውል

መደበኛ ዉል ማለት፤ ከፊሉ ወይም መላው ሁኔታዎቹ ለሁሉም ብዙ ውሎች የሚያገለግሉ ሁኔታዎቹ በአንዱና በቁጥራቸው ወይም በማንነታቸው ባልታወቁ ብዙ ሰዎች መካከል የሚያገለግል በአንደኛው ክፍል ብቻ የተወሰኑ አንድ ወጥ የውል ዓይነት ነው፤ ሻጩ ራሱ ባዘጋጀው ቅፅ ለዕቃ ገዢው የሚያመልክትበት በሁለቱ መካከል ያለምንም ድርድር(ትላልቅ ካምፓኒዎች በመገናኛ ክፍሎች፣ በባንኮች፣ የኃይልና በመሳሰሉት ካምፓኒዎች እንደሚታየው) ሻጩ ለገዢው የሚተሳሰርበት ቅፅ ነው፡፡

የአንድ ወጥ መደበኛ ውል ዓላማ ዕቃ ገዢዎችን ከሚጫኑ ሁኔታዎች ለመከላከል፣ ሁለት ተደራዳሪ ክፍሎች መካከል የዕውቀትና የኃይል ልዩነት መኖሩን በመረዳትና ብዙሃን ዕቃ ገዢዎች በዝቅተኛ ደረጃ ስለሚገኙም ነው፡፡

ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ ሁኔታ ዕቃ ገዢዎቹ ዝቅ ተደርገው እንዲታዩ የሚያደርግ ወይም ለሻጩ ተገቢ ያልሆነ ብልጫ መስጠት ዕቃ ገዢዎቹ ዝቅ ተብለው እንዲታዩ ወደ ማድረግ ይወስዳል፡፡ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ከሚያሳዩት ህጎች ትቂት ምሳሌዎች እነሆ፡

1. በህጉ መሰረት ያለዉን ሃላፊነት ዕቃ አቅራቢን ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርግ ቅፅ ወይም ተገቢ ባልሆነ መንገድ በውሉ ኃላፊነት ተጥሎበት እያለ የዚህ ሁኔታ መኖር ከኃላፊነቱ እንዲሸሽ የሚያደርግ
2. ለዕቃ አቅራቢው በቀላሉ መሠረዝ እንዲችል የሚያደርግን መብት የሚሰጥ፣ ማስተው ወይም የውሉን ተፈጻሚነት እንዲዘገይ ማድረግ ወይም እንደ ውሉ ግዴታዉን እንዳይዋጣ የሚያስተጓጉል
3. ዕቃ አቅራቢው ኃላፊነትን ወደ ሦስተኛ አካል ለማዛወር የሚያስችል ዕድል መስጠት
4. ከዕቃ አቅራቢው ቁጥጥር ውጭ ካልሆነ በቀር ከውል መፈራረም በኋላ ዕቃ አቅራቢው ዋጋን ወይም ከዕቃ ገዢው ላይ የተጣለውን\መሠረታዊ ግዴታ ሁኔታ መለወጥ የሚያስችል ሁኔታ መስጠት
5. በዋጋ መናር ምክንያት ከዋጋው ወይም ከሌላው ክፍያ ላይ ተጨማሪ ክፍያ እንዲደረግበት የዋጋው መውረድ ወይም ከፍ ማለቱ ደንበኛው ተጠቃሚ እንዳይሆን የሚወስን ሁኔታ።
6. ፍርድ ቤትና የአንድ ወጥ መደበኛ ውል ፍርድ ቤት የውል ልዩነት እንዳይኖር የሚያደርገውን ሁነታ መሠረዝ ወይም መለወጥ ይችላሉ፡፡

## የመክፈያ ዘዴዎችን በአግባቡ መጠቀም

### ቸኮች

ነጋዴዎች ቸክ የመቀበል ግዴታ ባይኖርባቸውም ተስፋፍቶ የሚገኝ የመክፈያ ዘዴ ቸክ ነው፤ ከዚህም ጋር ዕቃ ገዢው በቸክ በሚከፍልበት ጊዜ አንዳንድ መመሪያዎችን ልብ ማድረግ ይኖርበታል፤ ቸኩ ለሌላ ተላልፎ እንዳይሰጥ ዕቃ ገዢዎችን ለመከላከል የሚያስችል "ክሮስ"(ሁለት አግድም መስመሮች) ቸኩ ላይ ምልክት አለማድረግ የተለመደ ስህተት ነው፤ "የክሮስ"(ሁለት አግድም መስመሮች) ምልክት ትርጉሙ ይህ ቸክ ስሙ የተጻፈበት ሰው ብቻ ቸኩን ወደ ባንክ ቤት በመውሰድ ባንክ ቤት ማስገባት እንጂ ገንዘቡን ማውጣት እንደማይችል ነው፡፡ ቸኩን ወደ ገንዘብ ከመለወጥ ለመከላከል ከቸኩ ራስ ላይ "ለሙጣቭ ቢልባድ" ወይም ለተጠቃሚው ብቻ የሚሉትን ቃላት ወይም "ሎ ሳሂር" ከሚለው "ሽልሙ ለፐኩዳት" የሚለውን ለፐኩዳት የሚለውን መሠረዝ ነው፤ አስቀድመው የተዘጋጁ ቸኮችን ከባንክ ቤት ማዘዝ ይቻላል፡፡

አስቀድሞ ህጋዊ ምክር ሳንቀበል ቸክን መሠረዝ አይመከርም፤ ዕቃ ገዢው በልዩ ሁኔታዎች ብቻ ቸክን ይሠርዛል፤ ስለዚህ ቸክን ለመሠረዝ ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰዳችሁ በፊት ምክር መቀበል አስፈላጊ ነው፡፡

### ክሬዲት ካርዶች

**ዕዳዎችን መሠረዝ**

**የክፍያ ትዛዝን\ማስከፈሎች መሠረዝ**

በደፈናዉ: የክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች በዕቃ ገዢው ስለተከናወነ ገቢያ የወደፊት ክፍያዎችን ከመሠረዝ በቀር ክፍያን አይመልሱም፡፡ በክሬዲት ካርድ በተከናወነ ገቢያ ሦስት አካል አሉበት፡ የክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች፣ ዕቃ ገዢውና ዕቃ ሻጩ፡፡ የክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች ከሁለት ክፍሎች ጋር ስምምነት ስላለው ዕቃ ገዢው የሚያቀርበውን በማንኛውም ማመልከቻ የወደፊት ክፍያን ወዲያውኑ አይሠርዝም፤ ዕቃው ለገዛው ጭራሽ ካልደረሰ ለብድር ኩባንያዎች በማመልከት የወደፊት ክፍያውን ለማሠረዝ መጠየቅ ይቻላል፤ ዕቃው ለዕቃ ገዢው መድረሱ ክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች ግልፅ ቢሆን የካርድ ባለቤቱን መልሶ የማስከፈል መብት አለው፡፡

### ሠነድ የለሽ ግብይት

ሰነድ የለሽ ግብይት ማለት ዕቃ ገዢው ስለግብይቱ ሳይፈርም መረጃ ፊቱ ሳይቀርብ ከክሬዲት ካርዱ ላይ ግን ገንዘብ የሚወርድበት ሁኔታ ነው። ይህ ሁኔታ በስልክ፣ በኢንተርኔትና በመሳሰሉት በሚደረጉ ግብያዎች ይታወቃል። በዚህ ሁኔታ የካርድ ቁጥሩ ለሌሎች በመጥፎ ነገር ሊጠቀሙበት ለሚችሉ አካላት ይጋለጣልና ዕቃ የገዛው ሳይፈቅድ ላደረገው ግብይት ከሂሣቡ ገንዘብ ሊወረደበት ይችላል። ላላደረገው ገበያ ያለሰነድ ዕቃ የገዛ ገንዘብ እንደወረደበት ያወቀ ዕቃ ገዢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ለክሬዲት ካርድ ኩባንያዎች ማመልከት አለበት፡፡ ህጉ የክሬዲት ካርድ ኩባያዎች ገንዘብ መውሰድ በመሠረዝ ዕቃ የገዛው መልዕክት በመላክ ካሳወቀበት በ15 ቀን ውስጥ እንዲመልሱ ያዛል። ደንበኛው በስምምነት ገቢያ እንደተገበያየ ቢታወቅ የብድር ኩባንያው ከባለ ካርዱ መልሶ ገንዘብ የመውሰድ መብት አለው፡፡

**ያለፈቃድ የዋጋ ለውጥ ማድረግ፣**

በዚህ ሁኔታ ዕቃ ገዢው በካርዱ ከፍሎ ከተቀበለው ደረሰኝ በተጻፈው ዋጋና ከባንኩ ከወረደበት የገንዘብ መጠን ጋር እንደማይጣጣም ሲያውቅ፤ በዚህ ጊዜ የካርድ ኩባንያው በተቻለ ፍጥነት 30 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የዋጋውን ልዩነት ለዕቃ ገዢው መመለስ አለበት፡፡ ዕቃ ገዢው የገዛበት ዋጋና በተግባር የከፈለው ዋጋ ተመሳሳይ ከሆነ የካርድ ኩባንያው ገንዘቡን መልሶ ማስከፈል ይችላል፡፡

**ክሬዲት ካርድን ለመጥፎ መጠቀም**

ክሬዲት ካርድን በመጥፎ መጠቀም ማለት:  መብት የሌለው ሰው ካርዱን  ሲጠቀምበት ነው፤ የካርዱ ባለቤት እያወቀ ከሆነ ድርጊቱ ለመጥፎ እንደተጠቀሙበት አይቆጠርም። ጎልቶ የሚታወቀው ካርዱ ተሠርቆ ሌባው በካርዱ ሲጠቀምበት ነው። ካርድ የተሠረቀበት የካርድ ባለቤት ባስቸኳይ ለካርድ ኩባንያው ማሳወቅ አለበት። የተባለው መልዕክት ከተላለፈ በክሬዲት ካርድ ስለተደረገው ማንኛም ገቢያ ኩባንያው የካርዱን ባለቤት የራስ ተሳትፎ ማስከፈል ክልክል ነው፡፡ ከመልዕክቱ በፊት ለተደረገ ገቢያ  በህጉ መሠረት የካርዱ ባለቤት: እስከ 75 ሸኬል ካርዱ እንደተሠረቀ ከታወቀበት ጀምሮ ለካርድ ኩባንያ እስከተነገረበት ድረስ በየቀኑ 30 ሸኬል ጭማሪ በማድረግ የካርዱ ባለቤት ይከፍላል፤ ካርዱ እንደተሠረቀ ከታወቀበት በ30 ቀን ውስጥ መልዕክቱ ከተላለፈ የካርዱ ባለቤት ካርዱን ለመጥፎ በመጠቀም ከደረሰዉ ወጭ ከ450 ሸኬል በላይ አይከፍልም፡፡ ለካርድ ኩባንያው ካርዱን እንዳልተጠቀሙበት ከታወቀ ኩባንያው የካርድ ባለቤቱን ተመልሶ ማስከፈል ይችላል፡፡

## የመግዣ ቲኬት

በ2014 መጀመሪያ ላይ ስለመግዣ ቲኬት ዕቃ ገዢውን የሚከላከሉ ከ1/7/14 በሑዋላ የታተሙ የመግዣ ትኬቶች: አዲስ መመሪያዎች የግብር 36 ዕርማት ህግ ተደነገገ፤ አዲሶች መመሪያዎች ከዚያ በፊት ለወጡ የመግዣ ቲኬቶች ላይ አይከናወኑም፤ ዋና ዋና መመሪያዎች እነሆ:

**የመግዣ ቲኬቱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

ሀ. እያንዳንዱ የመግዣ ቲኬት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ይቆያል፡፡

ለ. የመግዣ ቲኬቱ ጊዜ እንዲያልፈበት ለመወሰን የሚፈልግ የመግዣ አታሚ፣ ጊዜው የሚያበቃው ከአምስት ዓመት በኋላ እንደሆነና ይህንም ለማድረግ ከመግዣ ቲኬቱ ላይ ጎልተው በሚታይ ፊደሎች ተጽፎ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

**ጎልተው በሚታይ ፊደሎች:**

1. የሚያወጣው ስም
2. መግዣ ቲኬቱ የወጣበት ጊዜ

**የመግዣ ቲኬቱ 100% – ተቀባይነት**

የመግዣ ቲኬቱን ሙሉ በሙሉ **100% እንዲቀበሉት እንጂ** በአንድ ቦታ **95%** ወይም **90%** ብቻ እንዲቀበሉት ማድረግ አይቻልም፡፡

**ከመግዣ ቲኬቱ መልስ**

ዕቃ ገዢው የመግዣ ቲኬት በመግዛቱ ሻጩ መልሱን በጥሬ ብር ሳይሆን በደረሰኝ ሊመልስ ይችላል፤ የመግዣ ቲኬቱ መልስ በሌሎችም ቅርንጫፎች ተቀባይነት ካለውና ተመሳሳይ የንግድ ስም ይዞ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

## በመግዣ ቲኬት የተገዛን ዕቃ መመለስ

በመግዣ ቲኬት የተገዛ ዕቃ ከተመለሰ ሻጩ የተገዛበትን ዋጋ በጥሬ ብር ሳይሆን መግዛት የሚያስችል ከመጀመሪያ ውሱን ካልሆነ በቀር ለመጠቀም ማንኛውም ዓይነት ወሰን የሌለበት የደረሰኝ(ቫዉቸር) የመስጠት መብት አለው፡፡

## የመግዣ መልስና ሥጦታ

ዕቃ ገዢ የገዛውን ዕቃ ወይም አገልግሎት ለመመለስ መሆን ያለባቸው ሁኔታዎች ባይሟሉም አልፎ አልፎ ሻጩ ከገዢው ጋር በመስማማት ለዕቃ ገዢው ገንዘቡን የሚመልስበት ሁኔታዎች አሉ፤ አብዛኛውን ጊዜ ገንዘቡን ለደንበኛው የሚመልሰው ዕቃ ማስገዛት በሚያስችል የደረሰኝ ነው፡፡

ዕቃ ማስገዛት የሚያስችለው ደረሰኝ የታተመ ወይም የተጻፈውን መሠረዝ በሚከለክል ሁኔታ መዘጋጀት እንዳለበት ህጉ ወስኗል፤ ዕቃ ማስገዛት የሚያስችለው ደረሰኝ ላይ የተጻፈው የገንዘብ መጠን በመገበያየቱ ጊዜ ከተከፈለው የገንዘብ መጠን ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት፣ ዕቃ ማስገዛት የሚያስችለው ደረሰኙ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ጸንቶ የሚቆየው ቢያንስ ለሁለት ዓመት ነዉ፣ የመግዣ ቲኬቱን ለመጠቀም የደረሰኝ ማሳየት አያስፈልግም: የደረሰኙን ተግባራዊ ለማድረግ በአንፃሩ የማያስችልና ቲኬቱን ለመጠቀም የሚገድብ ሁኔታ ተቀባይነት የለዉም(በልዩ ሽያጭ፣ ይህ መመሪያ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ካልነበሩት ቲኬቱን የሚገድብ መመሪያ የሚሰጥ ሥልጣን ካልነበረ በቀር)

## የበረራ አገልግሎትን በተመለከተ ልዩ መመሪያዎች

እላፊ ምዝገባ(ቦታ ኣላፊ ምዝገባ\ኦቨር ቡኪንግ) :የተሠረዘ በረራ፣ የዘገየ በረራ፣ ከጊዜው በፊት የቀደመ በረራ ወይም ሁኔታዎቹ የተቀየሩ በረራ) ሲፈጠር ደንበኛው ጥቅሞችንና ካሣዎችን የመቀበል መብት አለዉ፡፡

በዚህ መሰረት: የተተለያዩ ጥቅሞችና ካሳዎች: እነደ ክፍያውን ማስመለስ፣ የገንዘብ ካሳ: የአገልግሎት ዕርዳታ እንደሆኑ ህጉ ይወስናል፡፡

ከዚህ የተዘረዘሩት መመሪያዎች ተጓጓዡ ከገዛው ቲኬት ላይ ተግባራዊ የሚሆኑት እስከ መጨረሻዉ መድረሻ ድረስ በመንገድ ማሓል ማቆሚያ ቦታ ካለም፣ መመሪያዎቹ በሃገር ውስጥ በረራ ላይም ተግባራዊ ይሆናሉ:: መመሪያዎቹ ተግባራዊ የማይሆኑት: ቀደም ላለ በረራ ላይ በመተማመን: ለቀጣይ በረራዎች በተጓጓዡ ተናጠል በገዛው ቲኬት ላይ በተገዛ ትለኬት ይሆናል::

በመጀመሪያው ቲኬት ያልተጠቀሱ በቀጣዩ በረራ በበራሪው ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ወይም ለበራሪው ከሚደርሰው ጥቅሞችና ካሣዎች ከበለጡ ጉዳቶች: በራሪው ካሳ ለመቀበል በህጉ መሰረት ከሶ መጠቀም ይችላል፡፡

ጥቅሞችን ለመቀበል ተጓጓዡ በስዓቱ መገኘት(ቸክ ኢን) አለበት፤ "በስዓቱ "ማለት ኩባንያው በወሰነው ስዓት ማለት ሲሆን ግን ከበረራዉ ከሦስት ስዓት በላይ ወይም በፊት መሆን የለበትም፤ ስዓቱ ካልተወሰነ አንድ ስዓት ተኩል ከበረራዉ በፊት መሆን አለበት፤ ለተሠረዘ በረራ በስዓቱ የመድረስ ግዴታ የለበትም፡፡

በሚከተሉት ሁኔታዎች ጥቅሞችን የማስግኘት መብት ይነፍጋሉ፡

1. በራሪው ወደ ሌላ በረራ መተላለፉን መልዕክት ደርሶት በበረራ ካርዱ በተጻዉ ስዓት ካሰበበት ቦታ ከደረሰ።
2. በራሪው የበረራ ካርዱን በሥጦታ መልክ ከተቀበለ ወይም ለሕዝቡ በማይሸጥበት ልዩ ቅናሽ ዋጋ ከገዛ: ካርዱን በራሪው አባል በመሆኑ("የነጥብ ፕሮግራም") በሥጦታ ተቀብሎ ከሆነ ገደብ አያደርግበትም፤ ሌሎች ሁኔታች ለተጓጓዡ ከተሟሉ ጥቅሞችን የመቀበል መብት አለው፡፡

## ጥቅሞችና ካሣዎች

**ክፍያውን መመለስ**

**ክፍያ፡ ለበረራ የተከፈለ ክፍያ ሁሉ (ግብር ክፍያዎች: ቀረቶችና ልዩ ትዛዝ ክፍያዎች የመሳሰሉት)**

**መልሱ፡** የማስመለሻዉ ጥያቄ በቀረበ **በ**21 ቀን ውስጥ

በረራው ወይም አገልግሎቱ በከፊል ከተከናወነ፣ የሚከተሉት መመሪያዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡

ሁኔታው በረራ ከሆነ መንገድ ላይ እስኪያቆም ድረስ("ኮኔክሽን") ክፍያዉንና: በራሪው ወደ ተነሳበት መመለሻ የሚያስችል ቲኬትና ክፍያዉን የመቀበል መብት አለው፡፡

የደርሶ መልስ በረራ ከሆነ: "የደርሶ" በረራ ከተከናወነ በራሪው ከከፈለው ግማሹ ክፍያ ይመለስለታል፡፡

ቲኬቱ ከጉብኝት ጋር አብሮ የሚሄድ ከሆነና የቲኬቱን ዋጋ ለይቶ ለማወቅ የማይቻል ከሆነ እንደ በረራው ርቀት፣ ዓይነትና የሚጓጓዝበት ክፍል አገልግሎቱም(ይህ የመመሪያ መጽሄት እስከወጣበት ድረስ) ታስቦ ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

| ዓይነቱና ክፍሉ | እስከ 2,000 ኪ.ሜ | እስከ 4,500 ኪ.ሜ | ከ4,500 |
|---|---|---|---|
| ቻርተር/ የቱሪስቶች ክፍል | 780 ሸኬል | 1,550 ሸኬል | 2,590 |
| መደበኛ :የቢዝነስ ክፍል | 2,070 ሸኬል | 3,620 ሸኬል | 6,470 |
| መደበኛ :የመጀመሪያ ደረጃ | 4,140 ሸኬል | 7,240 ሸኬል | 12,940 |

**የገንዘብ ካሣ**

የገንዘብ ካሣ ለበራሪው የሚደርሰው ከሆነ ሊጓዝበት ያለው ርቀት (ይህ መመሪያ እስከወጣበት ጊዜ ትክክል የሆነ) ይታሰብለታል፡፡

| | |
|---|---|
| እስከ 2,000 ኪሎ ሜትር | 1,290 ሸኬል |
| እስከ 4,500 ኪሎ ሜትር | 2,070 ሸኬል |
| ከ4,500 ኪሎ ሜትር በላይ | 3,100 ሸኬል |

የገንዘብ ካሣው ከበረራው ጊዜ ጀምሮ በ21 ቀን ውስጥ በካሽ፣ በባንክ በማስተላለፍ፣ በቼክ ወይም በራሪው በግልፅ በጽሁፍ በተስማማበት ሌላ መንገድ ሁሉ ይከፈላል፡፡

**የጉዞ አገልግሎት**

| ምግብና መጠጦች | እንደ ጠበቀዉ ዘመን |
|---|---|
| የምኝታ አገልግሎት | በሆቴል ይህም: ከአንድ ሌሊት በላይ የበለጠ ወይም ተጓጓዡ ካሰበዉ በላይ ከተጉላላ |
| የጉዞ አገልግሎት | ከዚሁ ሆቴል ወይም በተገቢ ርቀት ላለ ተጓጓዢው የመረጠው ሆቴል |
| የመገናኛ አገልግሎት | እንደ ተጓጓዡ ምርጫ ሁለት የስልክ ንግግሮችና መልዕክት በፋክስ ወይም በኢ ጦማር(ኢሜይል) |

ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሞችና የሚሰጡበት ሁኔታዎች: ካሣዎች ዝርዝርና የትኛዎቹ ጥቅሞችና ካሣዎች ተጓጓዡ እንደሚደርሱት: በሚመጡት ዝርዝር ይገለፃሉ፡፡

## ካሣ እንዲደርስን የሚያደርጉ ሁኔታዎች

የበለጠ ምዝገባ(ኦቨር ቡኪንግ) ለዚህ ህግ መመሪያ ትርጉሙ ለደኅንነት፣ ለበረራው ደኅንነት፣ ለተጓዳኙ ጤንነት ወይም ተፈላጊው የበረራ መረጃ ባለመኖሩ ካልሆነ በቀር ተጓዳኙ የአየር ቲኬት እያለው ወደ በረራው እንዳይገባ የሚደረግ ማንኛውም ተቃውሞ::

በዚህ ሁኔታ ተጓዳኙ የበረራ አገልግሎት፣ የክፍያ ምላሽ ወይም የቲኬት ልዋጭና(እንደተጓዳኙ ምርጫ)፡ በተጨማሪም የገንዘብ ካሣ ይቀበላል:: ከበረራው ስዓት ቢያንስ ሦስት ስዓት ቀድሞ መገኘት፣ ትክክለኛ የበረራ ሠነዶችና ለደኅንነት ፍተሻ ተሳትፎ ማሳየት፡ ለደኅንነት ሲባል በሚደርስ ተቃውሞ የገንዘብ ካሣን ከመቀበል አያስቀርም::

ተጔጓዡ ልዋጭ በረራን ከመረጠ፡ የልዋጩ በረራ የማረፊያ ስዓት ከመጀመሪያው የበረራ ማረፊያ የመጨረሻ ስዓት አንፃር ተቀራራቢ ለሆነ (በረራው እስከ 2,000 ኪ.ሜ ከሆነ) ከአራት ስዓት በላይ የማያዘገይ፣ (በረራው እስከ 4,000 ኪ.ሜ. ከሆነ) አምስት ስዓት ወይም ስድስት ስዓት (በረራው 4,500 ኪ.ሜ. በላይ ከሆነ) የገንዘብ ካሣው በግማሽ ይቀንሳል፤ ሁሉም በተጓዳኙ የመጀመሪያው ስዓትና ማረፊያ ጣቢው አንፃር ይሆናል

### የተሠረዘ በረራ

የአየር መንገዱ ወይም የክራዩ(ቻርተር) ወደ መጨረሻ ማረፊያ ለመደርስ አማራጭ መስጠት ይኖርበታል::

የበረራውን መሠረዝ መልዕክት የማረጋገጡ ግዴታ የአየር መንገዱ ወይም የክራዩ(ቻርተር) ይሆናል::

በረራው ከተሠረዘ ተጓዳኙ ከአየር መንገዱ ወይም ከክራዩ(ቻርተር) የሚከተሉትን ካሣዎችን የመቀበል መብት አለው፡ የመጓጓዣ አገልግሎት፣ ክፍያውን ወይም ልዋጭ ቲኬት(እንደ ተጓዳኙ ምርጫ) ማስመለስና በተጨማሪም ታስቦ ለነበረው የበረራ ርቀት መሠረት የገንዘብ ካሣ

የልዋጩ በረራ የማረፊያ ስዓት ከመጀመሪያው የመጨረሻ የበረራ ማረፊያ ስዓት አንፃር ተቀራራቢ ለሆነ (ከአራት ስዓት በላይ የማያዘገይ (በረራው እስከ 2,000 ኪ.ሜ. ከሆነ) አምስት ስዓት (በረራው እስከ 4,000 ኪ.ሜ. ከሆነ) ወይም ስድስት ስዓት (በረራው 4,500 ኪ.ሜ. በላይ ከሆነ) ለተስማማ ተጓዳኘ የገንዘብ ካሣው በግማሽ ይቀንሳል፤ ሁሉም በተጓዳኙ የመጀመሪያው ስዓትና ከማረፊያ ጣቢው አንፃር ይሆናል::

በሚከተሉት ሁኔታዎች ተጓዳኙ የገንዘብ ካሣ አይደረግለትም፡

ሀ. ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ምክንያት በረራው ከተሠረዘ

- ከአየር መንገዱ ከክራዩ(ቻርተር) ቁጥጥር ውጭ ለሆነ ልዩ ምክንያቶች ደግሞም የቻሉትን ያህል ቢጥሩም በእነዚህ ልዩ ሰበቦች መሠረዙን ማስቀረት ያልተቻለ
- የስራ አድማ ወይም የፀጥታ ሥራ ማቆም
- ሰንበትን ወይም በዓልን ላለመሻር

ለ. በረራው መሠረዙን መልዕክት ለተጓጓዡ ከተሰጠው፡፡

- ከዋናው በረራ ጊዜ ቢያንስ 14 ቀን በፊት ፡፡
- ከዋናው በረራ በ7- 14 ቀን ውስጥ ለተጓጓዡ የቀረበዉ አማራጭ የበረራ ጊዜውን ከዋናው የበረራ ስዓት ከሁለት ሰአት የማያስቀድምና የመጨረሻውን የማረፊያ ስዓት ከዋናው የማረፊያ ስዓት ከአራት ስዓት በላይ የማያዘገየው ከሆነ፡፡
- ከዋናው በረራ ከ-7 ቀን በታች ለተጓጓዡ የቀረበው አማራጭ የበረራ ጊዜውን ከዋናው የበረራ ስዓት በአንድ ስዓት የማያስቀድምና የመጨረሻውን የማረፊያ ስዓት ከዋናው የማረፊያ ስዓት ከሁለት ስዓት በላይ የማያዘገየው ከሆነ፡፡
- የቀረበው አማራጭ በረራ አብሮ ሊጓጓዙ ላሉት ሁሉ መቅረብ አለበት፤ በተጨማሪም በቀረበው የበረራ አማራጭ እንዳይስማማ የሚያደርጉ የደኅንነት፣ የሃይማኖት ወይም የጤና ችግር መኖር የለባቸውም፡፡

**በረራ መዘግየት**

ከሁለት ስዓት በላይ፡ ምግብ፣ መጠጦች፣ መገናኛ፡፡

ከአምስት ስዓት በላይና ከስምንት ስዓት በታች፡ ገንዘቡን ማስመለስ ወይም ከመዘግየቱ የተነሳ ተጓጓዡ ላለመብረር ከመረጠ ልዋጭ ቲኬት፡፡

በነገታው ቀን፡ መኝታና መጓጓዣ፡፡

በረራው የዘገየው በሥራ አመፅ ወይም የፀጥታ አመፅ ምክንያት ከሆነ ለደንበኛው ምግብ፣ መጠጥና መገናኛ ዘዴ ብቻ ይደርሰዋል፡፡

**የአገር ውስጥ በረራ**

የተሠረዘው በረራ የሀገር ውስጥ በረራ ከሆነ ወይም ከሦስት ስዓት በላይ ከዘገየ ለደንበኛው ካሣ እንደሚከተለው ይከፈለዋል፡

| | |
|---|---|
| ከቴል አቪቭ(ስዴ ዶቭ) ቤንጉሪዮን አየር ማረፊያና ሐይፋና ኢላት መካከል | 250 ሽኬል |
| ከቴል አቪቭ(ስዴ ዶቭ) በዓይን የሃብ ወይም ሮሽ ፒና(ምሃናይም) | 150 ሽኬል |
| ማንኛውም ሌላ መስመር | 200 ሽኬል |

**በረራን ማስቀደም**

ከበረራው ቲኬት ላይ ከተጻፈው ጊዜ ከ14 ቀን በታች መልዕክቱ ከተሰጠ፡፡

- ከአምስት ስዓት በላይና ከስምንት ስዓት በታች የቲኬቱን ዋጋ ማስመለስ ወይም ልዋጭ ቲኬትን መቀበል፡፡
- ከስምንት ስዓት በላይ፣ የቲኬቱን ዋጋ ማስመለስ ወይም ልዋጭ ቲኬትን መቀበል፣ በተጨማሪም የገንዘብ ካሣ፡፡

**የበረራ ሁኔታዎች መለወጥ**

በበረራ ሁኔታን ለማሻሻል (ከፍ ወዳለ ክፍል) ተጓጓዡ እንዲከፈል አይጠየቅም፤ ደረጃ ዝቅ ላለ የበረራ ሁኔታ (ወደ ዝቅተኛ ደረጃ) ተጓጓዡ ከቲኬቱ ዋጋው ላይ ከ60% - 100% እንደሚከተለው ካሣ ይከፈለዋል፡

| | |
|---|---|
| ከመጀመሪያ ደረጃ ለቢዝነስ ክፍል | ከቲኬቱ ዋጋ 60% |
| ከቢዝነስ ክፍል ለቱሪስት ክፍል | ከቲኬቱ ዋጋ 80% |
| ከመጀመሪያ ደረጃ ለቱሪስት | ከቲኬቱ ዋጋ 90% |
| ከመጀመሪያ ደረጃ ለቱሪስት ከ4,500 ኪ.ሜ በላይ በረራ | ከቲኬቱ ዋጋ 100% |

በመንገድ ላይ ማረፍ ያለበት በረራን ጨምሮ ለያዘ በረራ ሁኔታዎች ዝቅ ካሉበት የበረራ ርቀት፤ ካሣው በአንፃሩ ይታሰባል፤ ቲኬቱ ከጉብኝት ጋር የተያያዘ ከሆነ የቲኬቱን ዋጋ ለመመለስ ከጉብኝቱ ጋር ተያይዞ ይታሰባል፡፡

## የማሳወቅና የዕርዳታ ግዴታዎች

የበረራ ከዋኝ ወይም አደራጅ ክፍል(በሕዝብ መቀበያና በኢንተርኔት ድኅር ገፅ) እና ከተጓጓዢ ወኪሎች(ኤጀንሲ)(በኢንተርኔት ድኅረ ገፅ) የበራሪን መብቶች ማሳየት እንዳለበት በህጉ ተወስኗል፡፡ እንዲሁም ለተጓጓዡ በህጉ መሰረት፡ የሚገባዉ መብት ካለ በፅሁፍ መብቱን የሚዘረዝር ሠነድንና በአየር ማረፊያ የመንገደኞች መብት አስከባሪ ባለስልጣ ተወካይ ማንነት ዝርዝር ስለመቀበል በህግ መመሪያ ተወስኗል፡፡

## የምሳሌ ካሣ

ለተጓጓዡ የዕርዳታ አገልግሎት ባለመቀበሉ ወይም ገንዘቡን በማስመለስ ወይም ከላይ እንደተብራራው የገንዘብ ካሣ ባለመቀበሉ ፍርድ ቤት ለተጓጓዡ የምሳሌ ካሳ እስከ 10,350 ሽኬል የመፍረድ መብት አለው፡፡

## የትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት

በንግዳዊ አካል ላይ ክስ ለመመሥረት የሚፈልግ ሸማች በተለያየ መንገድ ክሱን ማቅረብ ይችላል፤ መደበኛ ክስን በክሱ እንዲፈርድ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፤ በጠበቃ ቢያቀርብ ይመረጣል፤ በአብዛኛው የወረዳ ፍርድ ቤት(ቤት ሚሽፓት ሻሎም) ይሆናል። ተጨማሪ መረጃዎች በትናንሽ ፍርድ ቤቶች(ቤት ሚሽፓት ለትቢኦት ክታኖት) እንዲሁም በልዩ ልዩ ማብራሪያ አካላት ደንበኞች አገልግሎት ይገኛሉ፡፡

እነዚህ መሥመሮች እስከተጻፉበት ጊዜ ድረስ ከሳሽ በትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ከ33,800 ሼኬል ላልበለጠ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ክሱን ከማቅረቡ በፊት: ክሱን የማዘጋጀት ዕርዳታ ለመቀበል ወደ ትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ጸሐፊ ወይም የሸማቾች እርዳታ ድርጅቶች ጎራ ማለት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

### የታናናሽ ክሶች ፍርድ ቤት ሥልጣን

የትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ከሳሹ ባመለከተው ላይ ተወያይቶ የሚከተሉትን የመወሰን መብት አለዉ ፡ በገንዘብ ነክ ጉዳዮች፣ ምርትን ሻጩ እንዲቀይር ወይም እንዲጠግንና ገቢያን ሊሠርዝ ይችላል፡፡

### ከጠበቃ ጋር ወይም ያለጠበቃ?

በመመሪያው መሰረት ለሁሉም ክፍሎች፤ በልዩ ምክንያቶች ካልሆነ በቀር፤ የትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት በጠበቃ መገልገል አይቻልም፡፡

### የት ማመልከት ይቻላል?

በደንበኛውና በከሳሹ መካከል፤ ክስ የሚቀርብበት ቦታ በስምምነት ቢዉልም እንኳ፤ ደንበኛው ክሱን ከሚከተሉት ቦታዎች በትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ማመልከት መብት አለው:

- በመኖሪያ ቦታው ወይም በተከሳሹ የሥራ ቦታ፡፡
- ውል በተፈጸመበት ቦታ፡፡
- ኃላፊነቱ መከናወን ከነበረበት ቦታ፡፡
- ዕቃው ለገዥ በተሰጠበት ቦታ፡፡
- የክሱ መነሻ ጥፋት  ወይም ግድየለሽነት የተፈፀመበት ቦታ፡፡

### ግብር ክፍያ

በትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት ክስ ለሚመሠርት በጊዜው ህጉ የወሰነውን ግብር መክፈል አለበት፡፡

## የክሱ ደብዳቤ፣ የክስ መከላከያና የፍርድ ቤቱ ሂደት

በክስ ወረቀት: ከሳሽ ስሙን፣ መታወቂያ ቁጥሩን: የመኖሪያ አድራሻውን: እንዲሁም የተከሳሹን ስም፣ መኖሪያ አድራሻውን ወይም ሥራ ቦታውን መጥቀስ አለበት:: በኩባንያው ላይ ባቀረበው ክስ በአብዛኛው የንግዱን ባለቤት ወይም ወኪሉን በግል ተከሳሽ እንደሆኑ አያይዞ መክሰስ ስማቸውንና የመታወቂያ ቁጥራቸውንም(ለከሳሹ ከታወቁ) መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡

የኩባንያ ባለቤቶችን ወይም ወኪሎቹን ለመክሰስ ጥርጣሬ ቢኖር የሸማች እረዳት ድርጅት ጋር መማከር ይጠቅማል::

በክስ ወረቀት: የዉሉን አይነት: ዉሉ የተፈፀመበት ቦታና ቀን: ይገባኛል የሚሉትን መጠንና ክሱን የሚአፀድቁ ምክንያቶችን መግለፅ አለበት፡፡

ተከሳሽ: በ15 ቀን ዉስጥ: የክስ መከላከያ ወረቀት ማቅረብና: በቀጠሮ መቅረብ አለበት፡፡

ፍርድ ቤት: ሁኔታዉን ከሰማ በኋላ: በክሱ ላይ ይበይናል፤ አንዳንዴ ወደ ስምምነት እንዲመጡና ስምምነቱ የፍርድ ውሳኔ እንዲቀበል: ለሁለቱም ክፍሎች ይመክራቸዋል፡፡ ፍርድ እንደተሰጠ ሁሉም ክፍል ውሳኔው የሚለውን መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

## የይግባኝ ሥልጣን

በትናንሽ ክሶች ፍርድ ቤት በተፈረደው ላይ ይግባኝ ሊያቀርብ ለፈለገ ክፍል ፍርዱ ወደ እጁ ከገባበት በ15 ቀን ውስጥ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ይግባኝ ፍቃድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ለማንና የት ቦታ ማመልከት ይቻላል?

ዕቃ ገዢ ስለመብቶቻቸው ሊያመለክቱባቸው የሚችሉ ብዙ አካላት አሏቸው፤ ከፊሎቹ በልዩ ልዩ ክፍሎች ብቻ ሃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡ ከፊል ዝርዝሮች እነሆ:

| ስም | የግንኙነቱ ዝርዝር |
|---|---|
| ለዕቃ ገዢዎች መብት ተቆርቋሪና ለተገቢ ንግድ(ከጥር 2015 ጀምሮ የገዢዎችን መብቶች በሚጥሱት ላይ ትርጉም ያለው ቅጣት ለመቅጣት ለተቆርቋሪው ክፍል ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ | ቤት ሃድፋስ 12 , ኢየሩሳሌም<br>ቴሌፋክስ 02-5396012፣ ፋክስ 02-5672032<br>cpfta@moital.gov.il |
| የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት - አገር አቀፍ የምግብ አገልግሎት | ቴሌ: 08-6241010 ቴሌ: 03-6270100<br>ፋክስ: 02-5655969 |
| እንደ መንግሥታዊ የጤና ዋስትና ህግ መሠረት የተቀባይ ኮሚሽን | ቴሌ: *5400<br>ቴሌ: 02-5681234<br>ፋክስ: 02-5655969 |

| ስም | የግንኙነቱ ዝርዝር |
|---|---|
| ባንክ እስራኤል የባንኮች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን | ስልክ 02-6552680 ስልክ ,08-6552218<br>ፋክስ 02-6528805 |
| በገንዘብ መ/ቤት የዋስትናና የስቶክ ገቢያ ተቆጣጣሪ | ፋክስ 02-5695352 ስልክ *3002 |
| የእስራኤል መስፈ ተቋም | ስልክ 03-6465154 |
| የትምህርት መ/ቤት - የሕዝብ ጥያቄ ማመልከቻ | ስልክ 1-800-25-00-25 ፋክስ 02-5602390 |
| የፍት ሚኒስተር: የግል ጠበቃ ክፍያ አቅም የለሽ የሚረዳ | ስልክ:03-6932777 ስልክ:1-700-706-044<br>ፋክስ : 02-6467717 |
| የግንኙነት ሚኒስተር: በስልክና በኢንተርነት የሸማችን መብት ምርመራ እና አፈፃፀም | ስልክ፡03-5198231 ፋክስ፡03-5198106 |
| የኃይል ማመንጫ መ/ቤት - የነዳጅና የጋዝ አስተዳደር | ስልክ፡02-5316123 ስልክ፡ ,02-5006752 |
| የእስራኤል ፖስታ ቤት - የሕዝብ ጥያቄዎች ማመልከቻ | ስልክ፡1-700-500-171 ስልክ፡03-6303156 |
| የውኃ ባለስልጣን - የሕዝብ ጥያቄዎች ማመልከቻ | ስልክ፡03-6369602 ፋክስ፡ 03-7605702 |
| ለሕዝብ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለሥልጣን- የሕዝብ ጥያቄ ማመልከቻ | ስልክ፡ 02-6217111 ፋክስ: 02-6217122 |
| ሺ.ይ.ል ለዜጋ የምክር አገልግሎት | ስልክ፡ 1-800-50-60-60 |
| "ስሃር ሚፅቫ "- አቅም የሌላቸውን በፍርድ ውክልና መስጠት | ስልክ፡ 1-700-505-500 |
| የእስራኤል የሸማቾች ምክር ቤት | ስልክ፡ 1-700-727-888 ፋክስ:02-6241035 |
| የአካባቢ ጥራት መ/ቤት - የሕዝብ ጥያቄ ማመልከቻ | ኢየሩሳሌም 343370፣ ፖ.ሣ.5 ክናፌ ነሽሪም፣ 95464፣ ስልክ፡ 02-6495803/4 . |
| የሕዝብ ማመልከቻዎች ተወካይ፣ የመንግሥት ተቆጣጣሪ | ቤት ሃድፋስ 12፣ ፖ.ሣ.1081<br>ጊቭዓት ሻውል፣ ኢየሩሳሌም 9101001<br>ስልክ:02-6665000 02-6665204 |
| የኬብልና ሳተላይት ምክር ቤት | ስልክ: 02-6702210<br>ፋክስ: 02-6706373 |

# የሸማቾች ህጎች

በዚህ መመሪያ የቀረበው መረጃ ከዋና ዋና ህግጋት ላይና መመሪያዎችና ትዕዛዛት ላይ የተመሠረተ ነው:: ችግር ቢገጥማችሁ የሚመለከተውን ህግ ግልፅና በተብራራ ሁኔታ የተብራሩትን ህግጋቱንና መመሪያዎችን ማንበብ ይመረጣል:: ተጨማሪ ህግጋትን በሂስታድሩት ድኅረ ገፅ በ"ናቮ" የታረሙ ህግጋት ማጠራቀሚያ ልታገኙ ትችላላችሁ፡

- የስምምነት ህግ(ህግ ሲጣስ መድኃኒት) - 1970
- የኮንትራት ህግ ውል - 1974
- አንድ ወጥ መደበኛ ውል - 1972
- አንድ ወጥ መደበኛ ውል መመሪያዎች- 1983
- የሽያጭ ህግ - 1968
- የሽያጭ ህግ (ቤቶች)- 1973
- ሽያጭ ህግ (ቤቶች)(ለቤት ገዥዎች አስተማማኝ ዋስትና) - 1974
- የቤቶች ሽያጭ ትዕዛዝ(የዝርዝር ቅፅ) - 1974
- የሽያጭ ህግ መመሪያዎች(ለቤት ገዥዎች አስተማማኝ ዋስትና) (ወደ ሹም ሪፖርት)- 2008
- ያገለገለ መኪና ሽያጭ ህግ(መረጃን የማግኘት መብትና ግልፅነት) -2008
- የሕዝብ ጤንነት ትዕዛዝ(ምግብ) (አዲሱ ፎርም) - 1983
- የመሬት ይዞት ህግ(በጋራ ህንፃ ጋዝ አቅራቢን መቀየር) - 1991
- ጉዳት ለሚደርስባቸው ዕቃዎች የኃላፊነት ህግ - 1980
- የፍርድ ቤት ህግ(የተጣመረ ፎረም) –1984 (ክፍል ለ ምልክት ሠ በትናንሽ ክሶች የሚየገለግለው ህግ ቁጥር 59 ጀምሮ)
- በትናንሽ ክሶች የሚያገለግሉ የፍርድ መመሪያዎች(የፍርድ ሥርዓት) -1976
- የበረራ አገልግሎት ህግ(በረራን መሠረዝ ወይም የበረራ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ካሣና እርዳታ)- 2012
- የበረራ አገልግሎት ህግ መመሪያ(በረራን መሠረዝ ወይም የበረራ ሁኔታዎች በመለወጣቸው ካሣና ርዳታ)(የሃገር ውስጥ በረራ) - 2013
- ለሸማች የሚከላከል ህግ - 1981
- ለሸማች የሚከላከል ህግ መምሪያ (ገቢያን ማፍረስ) - 2010
- ለሸማች የሚከላከል ትዕዛዝ(የምግብ ምርቶችን ምልክት ማድረግና ዕሽጋ) - 1998
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች(ከሽያጭ በኋላ ኃላፊነትና አገልግሎት) - 2006
- ለሸማች የሚከላከል ትዕዛዝ(ምርት ላይ ምልክት ማድረግ) -1983
- ለሸማች የሚከላከል ትዕዛዛት(በመደበኛው ስምምነት የፊደል መጠን) -1995
- ለሸማች የሚከላከል ትዕዛዛት(ስለዳይመንድና ስለከበሩ ድንጋዮችና ሉል አስፈላጊ ግልፅ መሆን) -1995

- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (አገልግሎት በሚሰጠው እጅ ስላሉ ንብረቶች ግልፅ መሆን) -1993
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (ለዕውቅና የሚጣጣም ሥልጠና) -2002
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (ዕቃን ስለማስመለስ መመሪያን ማሳየት) -2005
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (ዓመታዊ ወለድን መጠን ማሰብ)  - 1983
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (የአንድ መለኪያ ዋጋ) -2008
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (ከእጅ ስልክ የሚወጣ የማይቆጠር ጨረር መረጃ) -2002
- ሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (በክሬዲት ሽያጭ፣ ልዩ አሻሻጥና  ሽቀጥ) -1983
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች (ገቢያን ለመሠረዝ ምክንያቶች)(መቀያየሪያ ዕቃ) -1986
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች(በጽሁፍ ውል ማዘጋጀትና ቸርቻሪው ለሻጩ መስጠት ያለበት ዝርዝር) -2008
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች(ከባንክ ያልሆነ የብድር ውሉ ዝርዝር ) -1989
- ለሸማች የሚከላከል መመሪያዎች(ማስታወቂያና ወጣቶችን ያነፃፀሩ ማስታወቂያና የሽያጭ መንገዶች ) -1991
- የወለድ(ዲቤት ካርዶች) ካርድን ስለማስከፈል ህግ-1986
- የወለድ ካርድን ስለማስከፈል መመሪያዎች-1986
- በምግብ ቅርንጫፍ ውድድርን ስለማራመድ መመሪያዎች(የዋጋዎች ግልፅነት)-2014
- የውሎች ህግ(አጠቃላይ ክፍል) -1973
- በምግብ ቅርንጫፍ ውድድርን ስለማራመድ ህግ -2014
- ሸማችን የመከላከል መመሪያዎች(የምግብ ምርቶች በቁጥጥር መሆናቸውን የማሳወቅ ግዴታ)-2012
-

## መ/ቤቱ ና ቅርንጫፎች

### ለሽማቾች የሒስታድሩት ድርጅት ባለሥልጣንዋና መ/ቤት

**ዋናው መ/ቤት፡** የአዲሱ ሂስታድሩት ቤት፣ አርሎዞሮብ 93፣ ቴል አቪቭ 6209801

**ለሕዝባዊ ጥያቄ ሰብአዊ መልስ፡**ከዕሁድ- ሐሙስ ከ10:00–12:00 በስልክ 03-6921280/1 ክፍለ አገራቱና ዕከላቶች:

| ክፍለ አገር | አድራሻ | የአጠናካሪው ስም | የፋክስ ቁጥር | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| ኢላት | ሜዲያን 1 ኢላት | ዓዲ ፒንላጥ-ሌቪ | 08-6372120 | 08-6372131 |
| አሽዶድ | ሽቢ ጺዮን 13፣ አሽዶድ | | 08-8531401 | 08-8512200 |
| አሽኬሎን | ቤን ጉሪዮን 1 አሽኬሎን | ኔፈሽ ይጽሐቅ | 08-6751492 | 08-6751489 |
| ብኤር ሸቫ - ደበቡብ | ዴሬኅ ይጽሐቅ ሬጌር፣ ፖ.ሣ. 627፣ ብኤር ሸቫ | ኢላና ቢቶን | 08-6463047 | 08-6463049 |
| ባት ያም | ሃሂስታድሩት 3 ባትያም | ሽሪ ሙክታር | 03-5069297 | 03-5064121 |
| ጊብዓታይም | ቫይጽማን 18 ጊብዓታይም | ጠበቃ ሊላኅ ካፐላን | 03-5730227 | 03-7318698 |
| ዲሞና | መዓፒሊም 9፣ ዲሞና | ሹላሚት ሌቪ | 08-6558081 | 08-6551121/2 |
| ሄዴራ | ቫይጽማን 47፣ሄዴራ | ያኢር ሻኢቢ | 04-6346632 | 04-6346630 |
| ሆሎን | ሃሂስታድሩት 54፣ ሆሎን | አርኖን ሻኡል | 03-5023355 | 03-5023342 |
| ሐይፋ | ሁሪ 2፣ ሐይፋ | ኒራ ሻሌቭ | 04-8620889 | 04-8610105 |
| ክኔሬት-ጢቤሪያ | ኅላኒ 4 ቲቤሪያ | መዓያ ኮሄን | 04-6715393 | 04-6791614 |
| ኢየሩሳሌም | ሽትራውስ 17፣ ኢየሩሳሌም | ዮሲ የሻይ | 02-6207279 | 02-6207225 |
| ሃሻሮን ሄርጼሊያ ክፋር | ሃባኒም 15፣ ሔርጼሊያ | ኤፍራት ሽሐር | 09- 7658116 | 09-7909406 |
| ካርሚኤል | ነሲኤይ ይስራኤል፣ 33 | ሔድቫ ቤትአን | 04-9987960 | 04-9987988 |
| ላይኛው ገሊላ/ነሃሪያ | ሃዓፅማዑት 1፣ ነሐሪያ | ሹሽ ቦጋኒም | 04-9829779 | 04-9827799 |
| ናታኒያ | ሬሜዝ 13፣ ናታኒያ | ጠበቃ ዮሴፍ መላኩ | 09-8627963 | 09-8627962 |
| ናጽሬት ዒሊትና ዓማኪም | ያራኒም 8፣ ናጼሬት ኢሊት | ሐያ ባርኮቢች | 04-6571528 | 04-6571527 |
| አራድ | አራድ | ኢላኒት አዙላዒ | 08-9954383 | 08-9957054 |
| ፔታኅ ቲክቫ | ሃሂስታድሩት 19፣ ፔታኅ ቲክቫ | ያኤል ሽምዖኒ | 03-9341886 | 03-9395908 |
| ላይኛው ገሊላ-ጽፋት | ጂቦቴንስኪ @ ጽፋት | ሐና ኤሊያስ | 04-6971638 | 04-6971637 |
| ርሾን ለጺዮን | ሮቺልድ 60፣ ርዕሾን ለጽዮን | ቪኪ ናይጎ | 08-9665969 | 03-9687069 |
| ረሆቮት | ሌቪን ኤፍሽታይን 24፣ረሆቦት | ጊናት ጊሚል | 08-9470776 | 08-9311700 |
| ራምሌ - ሎድ | ኤሊ ኮሄን 13፣ ሎድ | ማዛል ሒዩን | 08-9224188 | 08-9224971 |
| ራማት ጋን | ካሪቢፂ 6፣ ራማት ጋን | ኔሊ ሜሌኅ | 03-6727022 | 03-6720152 |
| ቴል አቪቭ | አሎዞሮቭ 93, ቴልአቪቭ | አሪኤላ | 03-6921834 | 03-6921177 |
| | | | | |

ההסתדרות

ביחד, בשבילך

**1-700-700-331**

**www.histadrut.org.il**